# የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ አቅድ ፡ (ቅንጅት) ።

ስቲቨን ፡ ሉወንሽቴን ፤
የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

## ሀ/ የሕጉ ፡ አቅዋም ።

፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ስለሞራል ፡ ጉዳዮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን [1] ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሌላም ፡ ጊዜ ፡ በየቦታው ፡ የሚገኙ ፡ ነገሥታት ፡ ኃይላቸውን ፡ በቀጥታ ፡ በሚነኩባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ረገድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ የሚቻለውን ፡ ቢያስከብሩም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በመሠረቱ ፡ አያሌ ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዓቶችን የሚመለከት ፡ ነበር [2] ። ኾኖም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡

1. በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ በአራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የተቋቋመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ መሠረታዊት ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ (የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፮) ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ክርስቲያን ፡ በነበሩት ፡ በመካከለኛውና ፡ በሰሜን ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታዎች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አገሪቱ ፡ ተስፋፍታ ፡ ብዙ ፡ እስላምና ፡ አረማዊ ፡ ሕዝቦች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ ሆነዋል ። እ. ኤ. አ. ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ከኤም ፐርሃም ፡ የተጻፈው ፡ ዘገቨርንሜንት ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት) ፡ እሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፻፭ ፡ ጀምር ፡ ተመልከት ።

2. የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ከወደቀ ፡ እንስቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በመናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ሆነው ፡ አገሪቱን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ሥር ፡ አድርገዋት ፡ በገዙ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቶችና በየጊዜው ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ኃይል ፡ አግኝተው ፡ ከመናገሻው ፡ ከተማ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ወጥተው ፡ ይገዙ ፡ በነበሩ ፡ ንጉሦች ፡ መካከል ፡ ሲወላወል ፡ ኖሯል ። በአሁኑም ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የአገሪቱ ፡ መሪ ፡ የሚጠራው ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥት" ፡ ማለት ፡ "የንጉሦች ፡ ንጉሥ" በሚል ፡ ማዕረግ ፡ ነው ። እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ፡ ኦቭዘርቨር ፡ አምስተኛው ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፻፶፪ ፡ "የአጼ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክን ፡ (ገድሉን) ፡ (፲፬፻፴፬ —፲፬፻፷፰)" ፡ እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ፡ ኦቭዘርቨር ፡ ስድስተኛው ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፳፫ ፡ የበዕደማርያም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክን (ገድሉን) ፡ (የ፲፬፻፷፰-፲፬፻፸፰)" ተመልከት ። በጠቅላላም ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከፐርሃም ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፳፱ ፡ ጀምር ፡ የሚለጥቀትን ፡ ከገጽ ፡ ፻፴፩ ፡ ጀምር ፡ የሚለጥቀትን ፡ ገጾችና ፡ እንዲሁም ፡ ሪቻርድ ፡ ፓንክረስት ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. እጻፈው ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ሒስትሪ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (የኢትዮጵያ ፡ የኢኮኖሚክ ፡ ታሪክ) ፡ እተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከ፲፱ ፡ ገጽ ፡ ጀምር ፡ ተመልከት ።

ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከገባበት ፡ እስከ ፡ ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተቀነባ በረ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አልነበረም ።

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በእስላም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ለሚኖሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መምሪያ፡ እንዲሆን፡ወደ ፡ ፲፫ኛው፡ መቶ ፡ ዘመን፡ ግድም፡ በግብፅ ፡ ውስጥ፡ የተጻፈ፡ መንፈሳዊና፡ ዓለማዊ ፡ ነገሮችን፡ የሚመለከቱ፡ ከልዩ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ በተራቀቀ፡ አኳኋን ፡ የተውጣጡ ፡ ሕጎች ፡ የተከማቹበት ፡ ነው [3] ። የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ሕጎችን ፡ ከሮማ ፡ ቤተክርስቲያንና ፡ ከእስላም፡ ትእዛዞች ፡ እንዲሁም ፡ ከኒቅያና ፡ ከአንጾኪያ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉባኤዎች ፡ ከተገኙ ፡ ውሳኔዎች ፡ ጋር ፡ አዋህዶ ፡ የያዘ፡ ሲሆን ፡ መጀመሪያ፡ በዐረብኛ፡ ተጽፎ [4] ፤ በኋላም ፡ ጥንታዊ ፡ ቋንቋ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተተርጉሞ፡ ክርስቲያኖች ፡ በሚኖሩባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ አማካይነት ፡ ይሠራበት ፡ ነበር [5] ። ስለወንጀሎች ፡ መጀመሪያ ፡ በሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ስለወንጀለኛ ፡ አቀጣጥ ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ እንደመደባለቅ ፡ ይላሉ [6] ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በሕጉ ፡ የተጻፉት ፡ የወንጀለኛ ፡

3. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ "ፀሐይ ፡ መቶ ፡ ሊታወንት" ፡ ማለት ፡ "በበልበቱ ፡ ምዕት"፡ ወይም፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች ፡ እንደተጻፈ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማድ ይነገራል ። በሰንትር ፡ ፍራንሲ ፡ ደ ፡ ድሩዋ ፡ ኮምፓሬ ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ታትሞ ፡ የወጣውን ፡ ከግራዚን ፡ የተጻፈውን ፡ አንትሮፖሎጂያ ፡ ልኮድ ፡ ፒናል ፡ ደ ፡ ለኤምፓይር፡ ዲኢቶፒ (ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ) ተመልከት ። የዚሁን ፡ የእንግሊዝኛና ፡ የአማርኛ ፡ ትርጉም ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷ ፡ እና ፡ ፪፻፹፯ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

4. ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከፐርፓም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፱ ፡ ተመልከት ።

5. አማናዚዮ ፡ ጉዲ ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ. ም. በኢጣልያ ፤ ወደኢጣሊያን ፡ ቋንቋ ፡ በተረጐመው ፡ በስተቀር ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አሁንም፡ ቢሆን፡ የሚገኘው ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ፡ ብቻ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥ ትን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ በማስተርጐም ፡ ላይ ፡ ነው ። ተርጓሚውም ፡ ባለ ፡ ፖለቲካል ፡ ሳይንስና ፡ ባለሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ዶክተር ፡ የሆኑት ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ፃድዋ ፡ ናቸው ።

6. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮችን ፡ የያዙ ፡ ክፍሎች ፡ ሲኖሩት ፤ የመጀመሪያው ፡ ክፍል፡ ስለ ሃይማኖት ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ነው ። በመሠረቱ (ፅዋዕትነቱ) ፡ ሃይማኖት ፡ ጠቀስ ፡ የሆነው ፡ የዚሁ ፡ ሥራ ፡ አቀነባበር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክፍ ሉም ፡ እንኳ ፡ ውስጥ ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ስግር፡ ይታያል፤ ለምሳሌ፡ የሚከተሉትን ፡ የምዕራፍ አርእስቶች ፡ እንመልከት ። ምዕራፍ ፡ ፵፩ ፡ "ታላቁን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለሚክድ ፡ ለሚያጥርድና ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ ለሚያመልክ ፡ የሚሰጥ ፡ ቅጣት" ። ምዕራፍ ፡ ፵፯ ፡ "ነፍስ ፡ መግደል ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት" ይላል ።

መቅጫ፡ ፅንስ፡ ሐሳቦች፡ ከጊዜው፡ ሥልጣኔ፡ በጣም፡ የቀረመዱ፡ ነበሩ ። [7]

የመጀመሪያው፡ ዘመናዊ፡ የተቀነባበረ፡ ጽሑፍ፡ ሕግ፡ ማለት፡ የ፲፱፻፴፫ቱ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ እስከታወጀበት፡ (ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ እስከ፡ ነገሡበት፡ ቀን)፡ እስከ፡ ጥቅምት፡ ፳፫፡ ቀን፡ ፲፱፻፳፫፡ ዓ. ም. ድረስ፤ ፍትሐ፡ ነገሥትና፡ በተለይም፡ ክርስቲያን፡ ባልሆኑት፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ግዛቶች፡ ውስጥ፡ የነበሩ፡ ልማዳዊ፡ ሕጎች፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ወንጀለኞች፡ የሚቀጡበት፡ ሕግ፡ ሆነው፡ ቆዩ። አዲሱ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ እንደ፡ ፍትሐ፡ ነገሥቱ፡ ሳይሆን፡ የማያሻሙ፡ ቅጣቶችን፡ በግልጽ፡ ለተጠቀሱና፡ ለተወሰኑ፡ ወንጀሎች፡ ይደነግጋል፤ ቅጣት፡ የሚወሰነው፡ የአጥፊው፡ ማዕርግና፡ ሐብት፡ ሰብአዊ፡ ባሕርይና፡ ዓላማ፡ እየታየ፡ ነበረ። የወንጀላቸው፡ መነሻ፡ "ሕገ፡ ወጥነት"፡ "ትዕቢት"፡ "ቅንዓት"፡ "ተንኰል"፡ "በቀል"፡ "ስግብግብነት"፡ "ጠበኛነት"፡ "ግደለሽነት"፡ "ጨቋኝነት"፡ የሆኑ፡ ወንጀለኞች፡ ቅጣታቸው፡ አነስተኛ፡ ሲሆን፡ ማዕረግና፡ ሐብት፡ ያላቸው፡ አጥፊዎች፡ ግን፡ ከሁሉ፡ የበለጠ፡ ከባድ፡ ቅጣት፡ ይወድቅባቸው፡ ነበር።

7. ዐውቆ፡ ስለማጥፋትና፡ በቸልተኝነት፡ ስለማጥፋት፡ ፅንሰ—ሐሳቦች፡ ፍትሐ፡ ነገሥት፡ እንደሚከተለው፡ ያትታል (ምዕራፍ፡ ፵፮)፤

ክፍል፡ ፩፡— የዱር፡ አውሬ፡ ለመግደል፡ ወይም፡ ለመምታት፡ እንጂ፡ ሌላ፡ ሰው፡ ለመግደል፡ ወይም፡ ለመምታት፡ ሐሳብ፡ ወይም፡ ፍላጐት፡ የሌለውን፡ ሰው፡ የሚመለከት። እንዲህ፡ ያለው፡ ሰውዬ፡ ሌላ፡ ሰውን፡ ቢገድል፤ ጉዳዩ፡ በሁለት፡ ዓይነት፡ አስተያየት፡ ይመረመራል። የመጀመሪያው፤ አደጋ፡ ሊደርስ፡ እንደሚችል፡ የሚያውቀውን፡ ነገር፡ ይመለከታል፤ .... ማለት፡ መሐል፡ ከተማ፡ ላይ፡ እተሰበሰቡ፡ ሰዎች፡ መካከል፡ አንድ፡ ወፍ፡ ወይም፡ የዱር፡ አውሬ፡ በር፡ ወይም፡ ርጦ፡ ሲደባለቅ፡ እያየበወቱ፡ ወይም፡ በአውሬው፡ ላይ፡ ቀስትን፡ እንደሚተኩስ፡ ያለን፡ ሰው፡ ነው። በዚህ፡ ዐይነት፡ ሁኔታ፡ ሰው፡ የገደለ፡ አንድ፡ ሰው፡ ፍላጐቱ፡ ሰው፡ ለመግደል፡ ባለመሆኑ፤ ... ያለፈቃዱ፡ ሰው፡ እንደገደለ፡ ሆኖ፡ ተቆጥሮ፡ ይፈረድበታል። ወንጀሉም፡ ዐውቆ፡ ወይም፡ ሆን፡ ብሎ፡ ከገደለ፡ ትንሹ፡ ገዳይ፡ ያነሰ፡ ነው። እንዲሁም፤ የአጥርን፡ ወይም፡ የቤቱን፡ ግድግዳ፡ ባለመቆጣጠር፡ ተንዶ፡ ሰው፡ ሲጎዳ፤ ከተ፡ ባሪያውን፡ ተናካሽ፡ አውሬዎቹን፡ ተራጋጭ፡ በቅሎዎቹንና፡ ግመሎቹን፤ ተዋጊ፡ በሬዎቹን፡ በደንብ፡ ሳይጠብቅ፡ ወይም፡ ተገቢ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ሳይሰጥ፡ እነዚህ፡ በሰው፡ ላይ፡ ጉዳት፡ ቢያደርሱ፡ ባለቤቱ፡ ያለፈቃዱ፡ እንዳጠፋ፡ ሆኖ፡ ተቆጥሮ፡ ይፈረድበታል። በመሠረቱም፡ ሕግ፤ ከአብጥሊስ፡ ምዕራፍ፡ ፵፰፡ ጋር፡ ከሚተካከለው፡ ምዕራፍ፡ ወደ፡ መጨረሻ፡ እንደተጻፈው፤ በመንገድ፡ ላይ፡ ጉድጓድ፡ ቆፍረው፡ ሳይደፍኑ፡ የተውና፡ ደረጃ፡ ሠርተው፡ ድጋፍ፡ ሳይሠሩለት፡ የቀሩ፡ ያለፈቃድ፡ እንዳጠፉ፡ ሰው፡ ይቀጣሉ። ሁለተኛው፡ ዐይነት፡ ደግሞ፤ ሲገሉ፡ መሞታቸውን፡ የማያውቁ፡ ሰዎችን፡ ይመለከታል፤ ማለት፡ ከብት፡ መታሁ፡ ብሎ፡ በድንገት፡ ሳያይ፡ ሰው፡ እንደሚመታ፤ ወይም፡ በበረሃ፡ ሰው፡ የለም፡ ብሎ፡ እንደሚተኩስ፡ የማይናገር፡ ጠንካራ፡ የመሰለውን፡ ግንብ፡ በድንገት፡ ሰው፡ ላይ፡ እንደሚናድ፡ ሰው፡ ያሉትን፡ ነው። ከዚህ፡ በላይ፡ በተገለጸው፡ ዓይነት፡ የተማታ፡ ወይም፡ የገደለ፡ ቅጣቱ፡ ከሀገር፡ መሰደድ፡ (መውጣት)፡ ነው፤ ከተ፡ ባሪያ፡ አደገኛ፡ አውሬ፡ እንዳለው፡ የማያውቅም፡ ሰው፡ ባሪያው፡ ወይም፡ አውሬው፡ ጉዳት፡ ባደረሰ፡ ጊዜ፡ ባሪያውን፡ ወይም፡ አውሬውን፡ ለተጐዳው፡ ዘመዶች፡ አሳልፎ፡ ከመስጠት፡ በስተቀር፡ ሌላ፡ ኃላፊነት፡ የለበትም። ጉድጓድ፡ የቆፈረውም፡ ደረጃ፡ የሠራውም፡ እንዲሁ፡ ከኃላፊነት፡ ነፃ፡ ነው። ከእሳ፡ አውሎስ፡ ፃድቅ፡ ወደ፡ እንግሊዝኛ፡ ቋንቋ፡ ተተረጐመ።

የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡ ተብሏል [8] ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ይህን ፡ ማረጋገጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ሕጐች ፡ ሲነፃጸሩ ፡ በተለይም ፡ እያንዳንዱን ፡ ወንጀልና ፡ ቅጣቱን ፡ በግልጽ ፡ በሚያትተው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ ይታይባቸዋል ። የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በጊዜ ፡ ቀደምትነት ፡ ካለው ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ቢሆንም ፡ ያልተብራራና ፡ በተወሰነ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡ የሆነ ፡ በደንብ ፡ የተገለጹ ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦችና ፡ ስለወንጀለኞች ፡ ውሳኔና ፡ አስተያየት ፡ የተሟላ ፡ አቀራረብ ፡ የጐደሉት ፡ ነበር ።

ከነፃነት ፡ መመለስ ፡ ወዲህ ፡ ባሉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጎች ፡ ከታወጁ ፡ በኋላ ፤ በሥልጣኔ ፡ የምትገሠግሠዋ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ አዲስ ፡ የተሟላ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መንደፍ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ግልጽ ፡ ሆነ ። በጀኔቫ ፡ (ስዊዘርላንድ) ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊቀ ፡ መምህርና ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የሆኑት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዦን ፡ ግራቨን ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲነድፉ ፡ አላፊነትና ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸውና ፡ ሥራው ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ተጀመረ ። ፕሮፌሰር ፡ ግራቨን ፡ በፈረንሣይኛ ፡ የጻፉትን ፡ ረቂቅ ፡ (አባን ፡ ፕሮዤ) የታወቁ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ለነበሩበት ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ (የሕግ ፡ አዘጋጅ) ፡ አስረከቡ ። ብዙ ፡ ውይይትና ፡ ማሻሻል ፡ ተደርጎ ፡ የመጨረሻው ፡ ጽሑፍ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፤ ሕጉ ፡ ወደ ፡ አማርኛና ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ [9] ፡ ተተርጉሞ ፡ ለፓርላማ ፡ ተሰጠ ። አዲሱ ፡ ሕግ ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸ

8. ከወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፤ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከጠቅላላ ፡ መሠረተ — ሐሳብ ፡ መካከል ፡ የሚከተሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠቅሳሉ ።

፲፩ ፡ ጌታችንም ፡ በወንጌል ፡ ብዙ ፡ የሚያውቅ ፡ በብዙ ፡ ይቀጣል ፡ ጥቂት ፡ የሚያውቅ ፡ ግን ፡ በጥቂቱ ፡ ይቀጣል ፡ ብሏል ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵፯ ።

፲፯ ። ሠለስቱ ፡ ምእትም ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ መጠን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ ሰውን ፡ መቅጣት ፡ እንዳይገባ ፡ አውቀው ፡ በሕፃንና ፡ በስካር ፡ በዕብድና ፡ በዝንጉ ፡ ከሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ በትልቅ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ለይተውታልና ፤ ይህም ፡ ደንብ ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ እንዲስማማ ፡ ነው ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፵፯ኛውን ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፫ ፡ ተመልከት ።

9. የሕግ ፡ መጽሔትና ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በይፋ ፡ በኦፊሲዬል ፡ የሚታተሙት ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ቢኖር ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ እንደአዛዥ ፡ የሚወሰደው ፡ የአማርኛው ፡ እትም ፡ ነው ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፭ ፡ የአዋጅ ፡ ቁ. ፪ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ክፍል ፡ ፳፪) ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሲረቀቅ ፡ የተጻፈው ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ፤ ይህንን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋዎች ፡ መተርጎምና ፡ በሦስቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ የተጻፉትን ፡ ማስማማት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ችግር ፡ እንደሚፈጥር ፡ በቀላሉ ፡ መገንዘብ ፡ ይቻላል ።

ውን ፡ ለማግኘት ፡ ከፓርላማ ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው፡ ቀረበና፡ በሐምሌ፡ ፲፰፡ ቀን፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ታውጆ ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ተደረገ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ፰፻፭ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ የደምብ ፡ መተላለፍ ፡ አንቀጾችን፡ ይዟል። ይኸ ፡ ሕግ፡ ከጥንት፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን፡ የሕግ፡ ልማድ [10] ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከወጡት ፡ ከአውሮጳ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ አዳዲስ ፡ ሕጎች ፡ አብዛኛዎቹን ፡ አዋሀዶ ፡ የያዘና ፡ የተራቀቀ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ከውጭ ፡ አገር፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ዋና ፡ ምንጮች ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፴፯፡ የወጣው ፡ የስዊዝ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የነበረው ፡ የሲዊዝ ፡ የሕግ ፡ ፍልስፍናና ፡ ዕውቀት ፡ (የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ጥናት ፡ ጁሪስ ፕሩደንስ) ፡ እንደሆኑ፡ ግልጽ፡ ነው [11] ። የሁለተኛነትንም ፡ ደረጃ ፡ የያዙ ፡ ሌሎች ፡ ምንጮች ፡ አሉ ፤ ከእነሱም፡ ቀዳሚ ፡ የሆኑ፡ የ፲፰፻፲፡ ( እ.ኤ አ. ) የፈረንሣይ ፡ የወ

10. ከኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ተወርሰው፡ አሁንም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው፡ ሕግ ፡ የሚገኙት ፡ ቅጣቶች ፡ ወንጀለኛ ፡ ለሌላው ፡ መቀጣጫ ፡ እንዲሆንና ፡ ወንጀሉን ፡ በመቀጣቱ ፡ እንዲክስ ፡ የሚያደርጉት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥርዐቶች ፤ የሞትና ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ወንጀሎችና ፡ በጠቅላላ ፡ ክፍሉ ፡ የሚገኙ ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፤ እንደ ፡ መጸጸት ፤ በሕግ ፡ ላይ ፡ መሳሳትና ፡ ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ የሚያቃልሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ያሉ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቅሉ ፡ በአውሮፓውያኖችም ፡ ዘንድ ፡ ያልታወቁ ፡ ባይሆኑ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ የተወረሱ ፡ ናቸው ። እላይ ፡ የጠቀስነው ፤ ግራበን ፡ ከገጽ ፡ ፰፯ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ላይ ፡ የዚህ፡ እንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፺፫ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንዲሁም ፡ በዛ ፡ ግራቨን ፡ የተጻፉትን "ሽር ፡ አ፡ ኑቦው ፡ ድሮዋ ፡ ፔናል ፡ ኢትዮጲዩን ፡ ደላ፡ፐሉ፡ እንሲያን፡ አላ ፡ ፐሉ፡ ሬይሳንት፡ ሊጅስላሲዩ፡ ዱ ፡ ምንድ" ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ዴ ፡ ክሪሚኖሎጊ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስቴክኒክ ፡ ፳ኛ፡ ቦልዩም፡ ገጽ ፡ ፪፻፺ — ፺፱ ፡ (እ.ኤ. አ. ፲፱፻፷፩) ፡ እና ፡ "ለኢቶፒ ፡ ሞደርን ፡ ኤሳ ፡ ኮዲፊካሲዮ ፡ ዱ ፡ ንቨውድርዋ" ፡ ሪቪ ፡ ፔናል ፡ ስዊስ ፡ ፸፱ኛ ፡ ቦልዩም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፯-፬፻፭ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፬) ፡ ተመልከት ።

11. በፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉትን ፡ የኢትዮጵያንና ፡ የስዊዝን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍሎች ፡ በጥንቃቄ ፡ ሲያስተያዩአቸው ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረቱ ፡ የስዊዝ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ልዩነቱም ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ይህ ፡ ልዩነት ፡ የመጣው ፡ የሲዊዝ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ግብራሪያ ፡ ጽሑፎችና፡ የሕግ፡ ሳያንስ ፡ ትምህርት ፡ ከወሰዱት ፡ እርምጃ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ኤፍ . ዙር ቸር ፡ ኮድ ፡ ፔናል ፡ ስዊስ ፡ ኤክስፖዜ ፡ ደሞቲፍ ፡ ደላቫ ፡ ፐሮዥ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ጽፎ ት ፤ ኤ . ጉቲየር ፡ በ፲፱፻፳ ፡ (እ . ኤ . አ .) ወደፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ፡ የተረጎመውን ፤ ፒ ሎጉዝ ፡ ኮሜንቴር ፡ ዱ ፡ ኮድ ፡ ፔናል ፡ ሲዊዝ ፡ (በስዊዝ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ሐተታ) በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፤ ቶርማንና ፡ ፎን ፡ ኦፈርርቢክ ፡ ሽዋይትዘርሽስ ፡ ሽትራፍ ፡ ጌሴትስቡኽ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፲፱፻፵ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፉትንና ሐፍተር ፡ ሌርቡኽ ፡ ዴስ ፡ ሽዋይትዘርሽን፡ ሽትራፍሬክትስ፡ አለገማይለር ታይል በሚል አርእስት በ፲፱፻፵፮ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፡ ተመልከት ።

ንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ( በጠቅላላ ፡ አዘገጃጀት ፡ ረገድ) ፡ [12] የ፲፱፻፶፩ ፡ ( እ. ኤ. አ. ) የዩጐዝላቪያ ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ (በወታደራዊ፡ ወንጀሎችና ፡ በመሠረት ፡ ሐሳቦች ፡ በኩል) ፤ በተጨማሪም ፡ የኖርዌ ፡ (፲፱፻ ፪ ፡ እ. ኤ. አ. )፥ የጣሊያን (፲፱፻፴ ፡ እ. ኤ. አ. ) ፥የግሪንላንድ( (፲፱፻፶፬ ፡ እ. ኤ. አ. ) የብራዚል ፲፱፻፵ እ. ኤ. አ. ) እና ፡ የግሪክ ፡ (፲፱፻፶ ፡ እ. ኤ. አ. ) ሕጐች ፡ ናቸው ። [13]

የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ውይይት ፡ ሲያደርግ ፡ ከተጻፉት ፡ ማስታወሻዎች [14] ፡ ሌላ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፤ ሕግ ፡ ለመሆን ፡ እንዴት ፡ እንደበቃ ፡ የሚገልጽ ፡ ምንም ፡ ያህል፡ የተጻፈ፡ ታሪክ ፡ የለውም ። አርቃቂው ፡ ሕጉን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ የተጠቀሙበትን ፡ ማስታወሻ ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ ለወጣው ፡ ጽሑፍ ፡ ምንም ፡ መግለጫ ፡ አልሰጡም ። እንደዚሁም ፡ አብዛኛዎቹ፡ የፓርላማ፡ መዝገቦች ( ቃለ ፡ ጉባኤ) ፡ አይገኙም ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በአዲስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የሚያሻሙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዴት ፡ መተርጐም ፡ ይገባቸዋል ፤ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጠራል ። የኢትዮጵያ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ ቁ. ፪ ፡ የሕግ ፡ ትርጓሜ ፡ አጋጊው ፡ (ሕግ ፡ ሰጪው) ፡ "ሕጉን ፡ ለመስጠት፡ በፈለገው ፡ ስሜት ፤ ሊደርስበት ፡ ካሰበው፡ ግብ" ፡ እና ፡" በሕጉ ፡ መንፈስ" ፡ መሠረት፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ይወስናል ። ሕጐች ፡ እንዴት ፡ እንደሚተረጐሙና ፡ ጽሑፎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚብራሩ ፡ ከሚወስኑ ፤ በብዙም ፡ ተቀባይነትን ፡ ካገኙ ፡ ሐሳቦች [15] ፡ በስተቀር ፡ የስዊስ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ በሆነበት ፡ ሥፍራ ፡ የስዊስ ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ፍልስፍናና ፡ ገላጭ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ እንደ ፡ ከፊል ፡ የአጋጊ ፡ ፍላጐት ፡ ተቆጥረው ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ መተርጐሚያ ፡ ያገለግሉ ፡ ይሆን ፤ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይቀራል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ጠቅላላው ፡ ሐሳብ ፡ በአስገዳጅነት ፡ ሥልጣን ፡ ባይሆንም ፡ በአግባቢነት ፡ መንፈስ ፡ የስዊስን ፡

12. የፈረንሣይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከፍተኛ ፡ ወንጀሎች ፡ ጥፋቶችና ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ በሦስት ፡ የተከፈለ ፡ ሲሆን ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሳይከተል ፤ ከፍተኛ ፡ ወንጀሎችንና ፡ ጥፋቶችን ፡ አጠቃልሎ ፡ መጀመሪያ ፡ ታላቅ፡ ክፍል ፡ ፪ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ በመባልና ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ኮንትራቬንሲዮ)፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ ተከፍሏል ።

13. ፒ. ግራቨን ፡ <u>አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ፡ ኢትዮጵያን ፡ ክሪሚናል ፡ ሎው</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፲፱፻፷፭ . (እ . ኤ . አ. ) የጻፈውን ፡ ተመልከት ። ሚስተር ፡ ኢስ ፡ ቴዲሺ ፤ በ፲፱፻፷፩ ፡ (እ. ኤ.አ.)በሚያወጣው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የኢጣሊያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቃሚ ፡ የአውሮፓዊ ፡ ነቅዕ ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ አቅርቧል ።

14. እነዚህ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ልጅ ፡ ኤም . ፊሊፕ ፡ ግራቨን ፤ በፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፈው ፡ የተያዙ ፡ ሲሆኑ ፡ እሁንም ፡ ገና ፡ አልተተሙም ።

15. ከሾችኖቪች ፡ <u>በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም.) "በአዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ትርጉም (ፍች) በኢትዮጵያ" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የጻፈውን ፡ ተመልከት ። የአማርኛው ፡ ትርጉም ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፱ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ፍልስፍና ፡ በሙሉ ፡ ከመቀበል ፡ አንስቶ ፡ ጭራሹን ፡ የስዊስ ፡ ምንጮችን ፡ ችላ ፡ እስከማለት ፡ ቢለያይ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ አንድ ፡ ተግቢ ማዕከላዊ ፡ ይዞታ ፡ እንደሚገኝ ፡ ያምናል ።

በስዊስ ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ በባለሥልጣኖች ፡ የተሰጠ ፡ መምሪያና፡ ስለሕጉ ፡ አወጣጥ ፡ የተጻፈ ፡ ታሪክ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ተመሳሳይ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሲነፃጸሩ ፡ የስዊስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ከሆነና ፡ የሕግ ፡ አርቃቂው ፡ ፍላጐት ፡ ሕጉ ፡ ሲወጣ ፡ የተደረገው፡ ክርክር ፡ ኔምብዛም፡ በመሆኑ ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ፍላጐት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊቆጠር ፡ ስለሚችል ፡ ከዚህ ፡ ፍላጐት ፡ እዛብቶ ፡ ለመተርጐም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ መስፋፋት ፡ እርምጃና ፡ የሐገሪቱን ፡ ልዩ ፡ ፍላጐት ፡ የሚመመለከቱ ፡ ደምበኛ ፡ ምክንያቶች፡ ካልቀረቡ ፡ በስተቀር ፡ ለስዊስ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ መሰጠት ፡ ይገባዋል ። የሕግ ፡ አርቃቂውም ፍላጐት ፡ በይበልጡን ፡ የሕጉ ፡ ትርጉም ፡ በስዊስ ፡ እንዳለው ፡ እንዲሆን ፡ መሆኑን ፡ ማሰብ ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊና ፡ ማኅበራዊ ፡ ፍላጐት ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ አፍራሽ ፡ ምክንያቶች ፡ ከሌሉ ፡ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የነበረውን ፡ የስዊስን ፡ ትርጉም ፡ መከተል ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ ግምት፡ ይፈጠራል።

የስዊስ ፡ ታሪክና ፡ ዘመናዊ ፡ መስፋፋት ፡ ከኢትዮጵያው ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ቢሆንም ፡ ይህን ፡ ዓይነቱ ፡ አስተያየት፡ ለሕጉ፡ አተረጓጎም ፡ የተወሰነ ፡ እርግጠኛነት ፡ ሊያስገኝና፡ ዳኞችም፡ እንዳሻቸው፡ እንዳይፈርዱ፡ ለመቆጣጠር ፡ ያስችላል ።

ይኸንን ፡ በምሳሌ ፡ ለመረዳት ፡ ሳይቻል ፡ አይቀርም ። "ሊፈጸም ፡ ስለማይቻል ፡ ወንጀል" ፡ በሚናገረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቁ. ፳፱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ሊፈጸም ፡ በፍጹም ፡ የማይቻል ፡ ከሆነ ፡ ፈራጅ ፡ ቅጣቱን ፡ እንዲያቃልል ፡ ይፈቀድለታል ። "ፍጹም፡ የማይቻል" ፡ ምን ፡ ፡ማለት፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ፡ አይደለም ፤ ስለ ፡ ጉዳዩም ፡ በሕግ፡ አውጭው፡ የተሰጠ ፡ ሐተታ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ የነዚህን ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፡ ዳኞች ፡ እንዲፈጥሩ ፡ ከመፍቀድ ፡ ይልቅ ፡ በስዊስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቃላት ፡ እንዳሉ ፡ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የነበሩትን ፡ የስዊስን ፡ ጽሑፎች ፡ ማመሳከር ፡ ያስፈልጋል ። "በፍጹም ፡ የማይቻል" ፡ የሚሉት፡ ቃላት፡ በስዊስ፡ ሕግ፡ ተመሳሳይ ፡ አንቀጽም ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ።[16] የስዊስ፡ የሕግ ፡ ዕውቀትና ፡ መግለጫ ፡ ጽሑፎች ፡[17] ሲመ

16. የስዊዝ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ.፳፫ ።

17. እላይ ፡ የሰጠነውን ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ.፲፩ ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ ሬቡይ ፡ አፌሲያል ፡ ፳፯ ፡ አራተኛ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፫ ፡ ዦርናል ፡ ደ ፡ ትሪቪዮና ፡ እ. አ. አ.) ፲፱፻፶ ፡ ገጽ ፡ ፳፮ ፡ ሬቡይ ፡ አፌሲየል ፡ ፳፰ ፡ አራተኛ ፡ ገጽ ፡ ፪፶፮ ፡ ዦርናል ፡ ደትሪቢዩን ፡ (እ. አ. አ.) ፲፱፻፶ ፡ ገጽ ፡ ፪፰ ፡ ሬቡይ ፡ አፌሲየል ፡ ፳፫ ፡ አራተኛ ፡ ገጽ ፡ ፪፴፪ ፡ ዦርናል ፡ ደ ፡ ትሪቢዩን ፡ (እ. አ. አ.) ፲፱፻፶፰ ፡ ገጽ ፡ ፪ ፡ እና ፡ ኤም ፡ ቫይብሊንገር ፡ "ላቴንታቲቭ ፡ ፫ኛ" በሚል ፡ አርእስት ፡ ሬቪ ፡ ፔናሲክ ፡ ስዊስ ፡ ቁ. ፩፻፳፪፪፩ ፡ ኦክቶበር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ (እ. አ. አ.) ውስጥ ፡ ተመልከት ።

ሬምሩ ፡ "ፍጹም" ፡ "ከተመዛዛኝ" ፡ ከማይቻል ፡ ጋር ፡ የተነጻጸረ ፡ መሆኑን ፡ ይረዷል ፡፡ አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁናቴዎች ፡ በአንዱ ፡ ክፍል ፡ ሲመደቡ ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ ይመደባሉ ፡ አጥጋቢ ፡ የሆኑ ፡ ተቃራኒ ፡ ምክንያቶች ፡ ካልኖሩ በቀር ፡ ለነዚህ ፡ ቃላት ፡ በስዊስ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ትርጉም ፡ መቀበል ፡ ይገባል ፡፡ ፍጹም ፡ እንደማይቻል ፡ ሳያውቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ ቢሞክርና ፡ ቢያቅተው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወንጀሉ ፡ በማንም ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ቢሆን ፡ የሞከረው ፡ ውስጣዊ ፡ ሐሳብ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞት ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ እንደቻለው ፡ ሰው ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ፡፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀለኞች ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቁ ፡ የማድረግ ፡ ተግባር ፡ እንዲስፋፋና ፡ እንዲያድግ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወንጀሉን ፡ እንደፈጸሙ ፡ ያህል ፡ እንዲቀጡ ፡ ያስፈልጋል ፡ ተብሎ ፡ ይታሰብ ፡ ይሆናል ፡፡ እነዚህ ፡ ምክንያቶች "ፍጹም" የሚለው ፡ ቃል ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ትርጉሜ ፡ እንዲያገኝና ፡ የወንጀሉ ፡ ለመፈጸም ፡ አለመቻል ፡ የሚያስገኘውን ፡ ከፊል ፡ መከላከያ ፡ እንዲወስን ፡ ያደርጋሉ ፡፡ እንደ ዚህ ፡ ያሉት ፡ ምክንያቶች ፡ የስዊስን ፡ የሕግ ፡ ዕውቀትና ፡ ፍልስፍና ፡ እንቀበል ፡ ከሚለው ፡ ግምት ፡ ያመዘኑና ፡ በፍጥነት ፡ የሚለዋወጠው ፡ የሕግ ፡ አቅድ ፡ እንዳ ስፈለገው ፡ እንዲንቀሳቀስ ፡ ይረዳሉ ፡፡

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲታወጅ ፡ የተደረገው ፡ ለአገሪቱ ፡ ብሔ ራዊ ፡ አንድነት ፡ ማጠንከርያና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለሚያደርጉት ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ መምሪያ ፡ እንዲኖር ፡ ነው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ሕዝቡ ፡ በጊ ዜው ፡ እንደዋና ፡ የማኅበራዊ ፡ ቁምነገር ፡ አድርጎ ፡ ከሚቆጥራቸው ፡ ነገሮች ፡ ከራቁ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ ይቆይና ፡ እንዲያውም ፡ የሚ ፈለጉት ፡ ማኅበራዊ ፡ ቁምነገሮች ፡ የቆሙበትን ፡ መሠረት ፡ የሚያፋልስ ፡ ይሆ ናል [18] ፡፡ ስለዚህ ፡ በሕግጋቱና ፡ በመስፋፋት ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ማኅበራዊ ፡ ቁምነገሮች ፡ መካከል ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፍጠር ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገ ባል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጠራል ፡፡

በዚህ ፡ ረገድ ፡ የአዲሱ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጀመር ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡፡ ከእሥር ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ዓመታት ፡ በሚያህል ፡ ጊዜ ፡

18. አንዳንድ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰሱ ፡ ፅንሰ - ሐሳቦች ፡ በተለይም ፡ ስለተበዳይ ፡ ፈቃድ ፡ በመላ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተንሰራፍቶ ፡ የሚገኘው ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ስለማድረግ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን ፡ የሚመለከት ፡ ለፈተና ፡ ስለሚሰጥ ፡ ጊዜ ፡ (ውሳኔውን ፡ ስለማገድ) ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለመፍታትና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ በልዩው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ወንጀሎች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አዲስ ፡ ናቸው ፡፡ ሌሎች ፡ መሠረተ—ሐሳቦች ፡ ደግሞ ፡ እንደ የዳኝነት ፡ ሥልጣንን ፡ የወንጀል ፡ ሥራን ፡ መሞከርን ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ መሆንን ፡ ማጥፋትን ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ አላፊነትንና ፡ የወንጀል ፡ ሥራዎችን ፡ መጣመርን ፡ የሚመለከቱ ፡ አዳጋች ፡ በመሆናቸው ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ ገና ፡ አልታወቁም ፡፡

ውስጥ ፡ የገዛራላቸውን ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብና ፡ ሕግጋቱም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉ ፡ የማይለዩትን ፡ ችግሮች ፡ ያጠኑና ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በብዛት ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እየተስፋፉ ፡ በሚሄድ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ማኅበርና ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ በሕዝቡ ፡ እንዲታወቅና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ ይረዳሉ ።

ይኸ ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። በአውሮጳ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ እንደሚደረገው ፡ ሕግጋቱን ፡ ለማሻሻል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ የሕግ ፡ ኮሚቴዎች ፡ በፍጥነት ፡ እያደገ ፡ ከሚሄደው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ ሕጎችን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ ሥራውን ፡ ያለማቋረጥ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ። በዳኝነት ፡ የሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ረገድም ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ይዞታ ፡ መፈጠር ፡ አለበት ። ሕጎችን (በተለይም ፡ ከአውሮጳ ፡ የመነጩትን ፡) ከሚለዋወጠው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ በቂ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። ቢሆንም ፡ ወደፊት ፡ ሕጉ ፡ የሚያስከትለው ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ለመተንበይ ፡ ዳኞችን ፡ እንዳሰኛቸው ፡ እንደዳይፈርዱ ፡ ለመከልከል ፡ እንዲቻል ፡ በሕጉ ፡ በኩል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ እርግጠኛነትና ፡ አቋም ፡ መኖር ፡ አለበት ። በእነዚህ ፡ ዘዴዎች ፡ አማካይነት ፡ አዲሶቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ሥራቸውን ፡ ከሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ በበለጠ ፡ እንደሚዛመዱና ፡ ለአገሪቱም ፡ ተለዋዋጭ ፡ ፍላጐቶች ፡ አስፈላጊውን ፡ መፍትሔ ፡ እንደሚያቀርቡ ፡ ተስፋ ፡ ተጥሎባቸዋል ።

## ለ/ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ አቅድ ፡ ውስጥ ፡ የቅጣት ፡ ዓላማዎች ።

የኢትዮጵያ ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ፍልስፍና ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ በማስፈራራትና ፡ በመበቀል ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ይበልጡን ፡ የተመሠረተ ፡ ይመስላል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቅጣት ፡ እንደአጥፊው ፡ ሁናቴና ፡ እንደጥፋቱ ፡ መጠን ፡ ልክ ፡ እንዲሆን ፡ በከፊል ፡ በማድረጉ ፡ "ክፉ ፡ ለሠራብህ ፡ ክፉ ፡ መልስለት (ሌክስ ፡ ታሊዮኒስ)" ፡ ከሚለው ፡ ሕግ ፡ የተሻለ ፡ እርምጃ ፡ ቢወስድም ፡ አንዳንድ ፡ ሌሎች ፡ አሰቃቂ ፡ ቅጣቶችንና ፡ የመበቀልን ፡ ሐሳብ ፡ የተደገፉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። እንደዚሁም ፡ የ፲፱፻፵፱

19. በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ በቁጥር ፡ ፫ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ፯) ቀጥሎ ፡ እንደተጻፈው ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ "የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ በሌሎችም ፡ በአንዳንድ ፡ መንግሥቶች ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ። በአገራችንም ፡ ወደፊት ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ፈቃዳችን ፡ ቢሆን ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ ለሞት ፡ ፍርድ ፡ የማያደርስ ፡ አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ወንጀል ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ በግርፋት ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀጡ ፡ እስካሁን ፡ የነበረውን ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ አጽንተን ፡ አቆይተነዋል" ።

ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እየአንዳንዱ ፡ ወንጀለኛ ፡ የአጠፋው ፡ ጥፋት ፣ ሰብአዊ ፡ ሁናቴውና ፡ አቅዋሙ ፣ ለጥፋቱ ፡ መነሻ ፡ የሆኑት ፡ ምክንያቶችና ፡ ወንጀሉን ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የአእምሮው ፡ ፍላጐት ፡ በይበልጥ ፡ እየ ታየ ፡ ቅጣቱም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እንዲሆን ፡ ቢያደርግም ፤ ወንጀለኞች ፡ ወደ ጥፋት ፡ እንደገና ፡ እንዳይመለሱ ፡ የማረም ፡ ፍላጐት ፡ አልተገለጸበትም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለተበዳይ ፡ ወገኖች ፡ ደኅንነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አሳቢነት ፡ ነበረው ። ብዙ ፡ ዘመናውያን ፡ የቅጣት ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ያጠኑት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቁ. ፲፰ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ —

ስለ ፡ ስድብና ፡ ስለበትር ፤ ስለ ፡ አካል ፡ ጉዳይ ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚከሰውና ፡ ስለ ፡ መቀጫ ፡ ለዳኝነት ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ዳኛው ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ከሚያስቀምጠው ፡ ከመቀጫው ፡ ገንዘብ ፡ ለተበዳዩ ፡ ከፍሎ ፡ በደለኛውን ፡ እሥሮ ፡ ሥራ ፡ እያሠራ ፡ ካሣውንና ፡ መቀጫውን ፡ ያስከፍል ። ለመጠባበቂያ ፡ የተቀመጠ ፡ የመቀጫ ፡ ገንዘብ ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

በመበቀል ፡ ላይ ፡ ቀድሞ ፡ የነበረው ፡ የከረረ ፡ ስሜት ፡ ዛሬ ፡ በመለወጥ ፡ ላይ ፡ ቢገኝም ፡ በቀልን ፡ የተመረኮዙ ፡ አንዳንድ ፡ ጸንተው ፡ የተመሠረቱ ፡ ቀዋሚ ነገሮች ፡ አሉ ፤ ከነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ ነው ። ከሰውነት ፡ ብልቶች ፡ አንዳንዱን ፡ በመቁረጥ ፡ ይፈጸም ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ ከተወሰኑ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ እንዲቀር ፡ ተደርጓል ። የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ ግን ፡ በ፲፱፻ ፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ ይገኛል ። የዚሁ ፡ ሕግ ፡ ንዳፊ ፡ መጀመሪያ ፡ ባዘጋጀት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ አላስገቡም ፡ ነበር ። የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንና ፡ ፓርላማ ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲጨመር ፡ አደረጉ ። የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ መጨመር ፡ በመደገፍ ፡ የተሰጡት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ከቅጣት ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ ተስማሚነቱ ፡ በጣም ፡ የሚያስቅቁ ፡ ወንጀሎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸም ፡ መሆኑና ፡ ሰዎችን ፡ ወደ ጥፋት ፡ እንዳይሔዱ ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ነው ።[20] ፓርላማ ፡ ብዙ ፡ ከተከራከረበት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ቁ. ፩፰ (ሀ) ፡ [21] ሁኖ ፡ ገባና ፡ ከባድ ፡ ስርቆትና ፡ (ቁ. ፮፻፴፭ ፡ (፫)) ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡ (ቁ. ፮፻፴፯ (፩)) ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሠራበት ፡ ተደረገ ። የጅራፍ ፡ ግርፋት ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ዕድሚያቸው ፡ በ፲፰ ፡ እና ፡

20. የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ የቃል ፡ ውይይት (ፕሮሴ ፡ ቬርባል) ፡ ሚያዝያ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ ገጽ — ፫ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ሐምሌ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ጁላይ ፡ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፤ የመጨረሻው ፡ ውሳኔ ፡ ሐምሌ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ጁላይ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ተመልከት ።

21. ፓርላማ ፡ የጨመረው ፡ መሆኑን ፡ ለማስታወቅ ፡ " ሀ " የሚል ፡ ተጨማሪ ፡ ያለው ፡ ቁጥር ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በ፶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ የሆነ ፡ ወንዶች ፡ አጥፊዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ግርፋቱ ፡ ከዓርባ ፡ ጅራፍ ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ። የሚፈጸመውም ፡ በሐኪሞች ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው ። ግርፋቱ ፡ የተቀጭውን ፡ ጤንነት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ሐኪሙ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ግርፋቱ ፡ እንዲያበቃ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ በማራዘም ፡ "የሕዝብን ፡ መንፈስ ፡ ጸጥታ ፡ የሚነሱ " ብሎ ፡ በመደባቸው ፡ ሰባት ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎችን ፡ በሚሠሩ ፡ ላይ ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምባቸው ፡ የሚያውጅ ፡ አንድ ፡ ድንጋጌ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ወጥቷል ።[22]

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ፋንታ ፡ ግርፋትን ፡ ለመተካት ፡ እንደሚችልና ፡ ቅጣቱም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፮ (ሀ) መሠረት ፡ እንዲሆን ፤ ግን ፡ ከ፵ ፡ ጅራፍ ፡ እንዳይበልጥ ፡ ድንጋጌው ፡ ይናገራል ። የሞትም ፡ ቅጣት ፡ ባዲሱ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አልቀረም ፤ ይኸ ፡ ቅጣት ፡ በስቅላት ፡ መፈጸም ፡ እንዳለበትና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከፈለገ ፡ ለሌሎች ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሆን ፡ ስቅላቱን ፡ በይፋ ፡ ለመፈጸም ፡ እንደሚቻል ፡ ሕጉ ፡ ይደነግጋል ። (ቁ. ፻፲፮ ) ። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልማድና ፡ የሕዝቡ ፡ ስሜት ፡ ነፍስ ፡ መግደልን ፡ እንደ ፡ ቤተሰብ ፡ ግል ፡ ጉዳይ ፡ ወደመቁጠርና ፡ የደም ፡ ካሣ ፡ በማስከፈል ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሟቹን ፡ በገደለበት ፡ ሁኔታ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩን ፡ <u>በመበቀል</u> ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቀር ፡ ወደማሰቡ ፡ ያዘነብላል ። እነዚህም ፡ ስሜቶች ፡ ጽኑ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከተገዳዩ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንዱ ፡ በተወሰነው ፡ ሥፍራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ የሰጠውን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በጠበንጃ ፡ ተኩሶ ፡ ለመፈጸም ፡ ይፈቀድለት ፡ እንደ ነበር ፡ ይነገራል [23] ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ በሆነና ፡ የተቀነሰ ፡ ኃላፊነት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ እንደማይደርስባቸውና ፡ ቁ. ፻፲፰ ፡ በልማድም ፡ ሆነ ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአን. ፴፭ ፡ መሠረት ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይስማማበት ፡ እንደማይፈጸም ፡ መታወቅ ፡ አለበት ።

22. የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ (የቅጣት ፡ ሕግ) ፡ ድንጋጌ፡ ቁ.፶፩። የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም ሕገ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፪ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕግ፡ ሆነው ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ፓርላማ ፡ ሳያጸድቃቸው ፡ ብቻውን ፡ ሊያውጅ ፡ ይችላል ፡ ይላል ። ይኸም ፡ የሚሆነው ፡ አማካሪዎች ፡ ባልተሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ መሆኑን ፡ ይኸው ፡ አንቀጽ ፡ ይገልጻል ። ፓርላማ ፡ በሚቀጥለው ፡ ስብሰባው ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ ሊያጸድቅ ፡ ወይም ፡ ሊሽር ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፤ ግን ፡ በዚህኛው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እርምጃ ፡ አልወሰደም ። ስለዚህ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይሠራበታል ፡ ብሎ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ።

23. ከላይ የተጠቀሰው ፡ ፐርሃም ፡ ገጽ ፡ ፻፶፱ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ።

የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. (እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፬-፷፭) ፡ ስታቲስቲክ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ፱፻፹፯ ፡ ሰዎች ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ሲጠበቁ ፡ ፴፱ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ተፈጽሞባቸዋል ። የዚሁም ፡ ምክንያት ፡ በከፊል ፡ ቅጣቱን ፡ ለመፈጸም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ቅልጥፍ ፡ የሥራ ክንውን ፡ ባለመደረጉ ፡ ሊሆን ፡ ቢችልም ፤ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ይቅርታንና ፡ ምሕረትን ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣኑን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚያደርገው ፡ ርኅራኄ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።[24] ምንም ፡ እንኳን ፡ መበቀል ፡ በተለይም ፡ ሰውን ፡ ወደጥፋት ፡ እንዳይ ፥ ድ ፡ ማስፈራራት ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እንዳስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ተቆጥረውና ፡ በጣም ፡ ጕልተው ፡ ቢታዩ ፤ አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ወንጀለኞችን ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ በተመላበትና ፡ ይበልጥ ፡ ዘመናዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ማስተናገዱ ፡ እየተቃረቡ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ከጉዳት ፡ እንዲጠበቁ ፡ ከደነገጋቸው ፡ ሌሎች ፡ መከላከያዎች ፡ መሐከል ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነና ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በማሠቃየትና ፡ ሰብአዊ ፡ ባልሆነ ፡ ቅጣት ፡ እንደማይቀጣ ፡ ይወስናል ፡ (አን. ፶፩ና ፡ ፶፯) ።

የ፲፱፻፵፱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ማስፈራራትን ፡ እንደ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ በማድረግ ፡ ቢያስቀርም ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግን ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስገብቷል ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ መቅድም ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ፤

--- ማናቸውም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ፍትሕን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እያደጉ ፡ የሚሄዱትን ፡ አዳዲስ ፡ አሳቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ የአሳብ ፡ ምርመራን ፡ የአቀጣጥን ፡ ዕውቀቶች ፡ ጨምሮ ፡ ማሰብ ፡ የተገባ ፡ ነው ። ተገቢ ፡ የሚሆነውንም ፡ ፍትሕንና ፡ ነፃነትን ፡ ወንጀልን ፡ መከላከልንና ፡ መጨቆንን ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲውል ፡ ማድረግን ፡ የያዙትን ፡ የመሠረታውያኑን ፡ ነገሮች ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ቅጣት ፡ ግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፤ ደግሞም ፡ "አጥፊ ፡ ሲቀጣ ፡ የሚያየው ፡ ብልህ ፡ ይሆናል" እንደተባለው ፡ ሁሉ ፡ ለሌላው ፡ አጥፊ ፡ ትምህርት ፡ እንዲሆነው ፡ ነው ።

24. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የዓመት ፡ ሪፖርት ። ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የምሕረት ፡ ወይም ፡ የይቅርታ ፡ ሥልጣን ፡ እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ. ፳፭ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

25. እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፳፮-፴፪ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

ቁ. ፩ ፡ የሕጉን ፡ ግብና ፡ ዓላማ ፡ ሲናገር ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግና ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሔድ ፡ ማድረግ ፡ የቅጣት ፡ ሕግ ፡ መሠረታውያን ፡ ዓላማዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ያረጋግጣል ።

በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ አያሌ ፡ ቁጥሮች ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግን ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። ዳኛው ፡ ቅጣት ፡ በመምረጥ [25] ፡ ረገድ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ የማድረግ ፡ ሰፊ ፡ መብት ፡ ተሰጥቶታል ፤ በተለይም ፡ በቁ. ፻፯ ፡ ዳኛው ፡ ቅጣት ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ እንዲያደርግ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰጥቶታል ፤—

> ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፤ ፡ ያጥፊውን ፡ ያደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ እንደመጠኑ ፡ በመገመት ፤ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ለማጥፋት ፡ ያነሣሡትን ፡ ምክንያቶችና ፡ ያሳቡን ፡ ዓላማ ፤ የግል ፡ ኑሮውን ፡ ሁኔታና ፡ የትምህርቱን ፡ ደረጃ ፤ እንዲሁም ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነትና ፡ ያፈጸመን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመገመት ፡ በራሱ ፡ አጥፊነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ መለኪያዎች ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳሉ ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ስለቅጣት ፡ መታገድ ፡ ለፈተና ፡ ስለሚሰጥ ፡ ጊዜና ፡ ለአመክሮ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለመፈታት ፡ ያወሳል ። ዘመናዊውንም ፡ መንፈስ ፡ በጣም ፡ በተደገፈ ፡ አነጋገር ፡ "ለአመክሮ ፡ የመልቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የተቀጭውን ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መመለሻ ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ ይገባዋል" (ቁ. ፪፻፮) ይላል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ ወጣቶች ፡ አጥፊዎች ፡ እንዲታረሙ [26] ፡ የተለየ ፡ ቅጣቶችን ፡ ለሚሠሩት ፡ ወንጀል ፡ ኃላፊነት ፡ የሌላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥ ፡ በሁለት ፡ በሁለትዓመት ፡ ቢደረግም (ቁ ፻፴፮) ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ቦታ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ያዝዛል ። የጥበቃው ፡ ጊዜ ፡ አለመወሰን ፡ አጥፊው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግ ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦች ፡ በተሟላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ይረዳል ። ሰውን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ ማስፈራራትን ፡ እንደዋና ፡ ዓላማቸው ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ተራ ፡ ቅጣቶች ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ ሊፈጽሙ ፡ አይችሉም ፤ ምክንያቱም ፡ ሕግ ፡ ሰጭው ፡ የያንዳንዱን ፡ ወንጀል ፡ አስጊነት በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ስለአደራጃቸው ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሳያልቅ ፡ መፈታት ፡ የሚገባው ፡ ቢሆንም ፡ እንደታሠረ ፡ መቆየት ፡ አለበት ፤ እንዱ ፡ ደግሞ ፡ ወንጀል ፡ እን

26. እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፱፭ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ቀናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

ደገና ፡ የመፈጸም ፡ አዝማሚያ ፡ ቢኖረውም ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ መፈታት ፡ አለበት ። የሆነው ፡ ሆኖ፣ ሁለቱም ፡ ሐሳቦች፣ ማለት ፡ ሰውን ወደጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ ማድረግና ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግ ፡ በሕጉ ፡ የተጉለጹ ፡ የቅጣት ፡ ግቦች ፡ መሆናቸውንና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አንዱ ፡ አንዱን፣ ለመጻረር ፡ እንደሚችል፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ።

ባዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ስለማድረግ ፡ የሚናገሩት ፡ ውሳኔዎች ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እርምጃ ፡ ተወሰዷል ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የመጀመሪያዎቹ፡ እሥረኞች ፡ ለእመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ እንዲፈቱ ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡ እሥር፣ ቤቶችን ፡ የሚቆጣጠረው፡ ያገር ፡ ግዛት ሚኒስቴርና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ የሚያዘው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አስተያየት ፡ የተለያየ ፡ ስለሆነ ፡ ችግር ፡ ተፈጥሮአል ። በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በእሥር ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የኅላፊነት ፡ መከፋፈል ፡ ሌሎች ፡ አከራካሪ ፡ ሁናቴዎችንም ፡ አስከትሏል ። ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ በፖሊሶች ፡ ተዘጋጅተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት የሚቀርቡት ፡ የወንጀለኛ ፡ ምርመራ ፡ መግለጫዎች ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፋይሎች ፡ ውስጥ ፡ ይቀራሉ ። ለእሥር ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሚሰጠው ፡ የወንጀለኛው ሙሉ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ሳይሆን ፡ የፍርዱ ፡ ዐይነትና ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የእሥረኞች ፡ አከፋፈል ፡ የሚስማማው ፡ ለፍርዱና ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ እንጂ እያንዳንዱን ፡ ወንጀለኛ ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ፡ ለማርካት ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተቋቋሙት ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ሰውነት ፡ ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግ፡ የተቀደሱ፡ ሐሳቦች፡ በሚያጠግብ፡ ሁኔታ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ የፍርድና ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዓት ፡ አቅጣጫውን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ እንዲለውጥ ፡ ያስፈልጋል ።

## ሐ/ አካለ መጠን የደረሱ ወንጀለኞች ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስለደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ቁጥርና ፡ ዐይነት (ስታትስቲክስ) በየቦታው ፡ ባሉት ፡ የፖሊስ ፡ ክፍሎች ፡ ተሰብስበው ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ተከማችተው ፡ የሚገኙት ፡ ብቻ ፡ ናቸው። እነሱም ፣ ምንም ፡ እንኳ ፡ በፋፊ ፡ አዝማሚያዎችን ፡ እንደሚያሳዩ ፡ እምነት ፡ ሊጣ

ልባቸው ፡ ምናልባት ፡ ቢቻልም ፤ ያልተሟሉ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ስሕተት ፡ ሳይገኝባቸው ፡ አይቀርም ። [27]

በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፮ — ፷፯ ስታትስቲክስ ፡ የተሠራለት ፡ የመጨረሻው ፡ ዓመት) ፹፰ሺ፰፻፶፱ ተከሳሾች ፡ እንደተፈረደባቸው ፡ ተገልጧል ። ከነዚህም ፡ ፳ሺሕ፯፻፺፰ቱ በንብረት ፡ ላይ ፡ በፈጸሙት ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ፩ሺሕ ፩፻፷፰ቱ ሆነብለው ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ነበር ። በንብረት ፡ ላይ ፡ የተፈጸሙት ፡ የወንጀሎች ፡ ብዛት ፡ ከተጠቀሰው ፡ ሳይበልጥ ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ይዞታ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ አያሌ ፡ ወንጀሎችን ፡ የሚያመለክት ፡ አኃዝ ፡ ባለመስጠቱ ፡ ነው (ቁ. ፩፻፵፱ - ፶፪) ። አብዛኛዎቹ ፡ ወንጀሎች ፡ የተፈጸሙት ፡ በሸዋና ፡ በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። የከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ በብዛት ፡ ተከማችተው ፡ በሁለቱ ፡ ስለሚገኙ ፡ ይኸ ፡ አያስደንቅም ።

አካለ ፡ መጠን ፡ በደረሱ ፡ አጥፊዎች ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎቹ ፡ የሚገኘው ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ርዝራዥና ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ የማይቻል ፡ በመሆኑ ፡ ለወንጀሉ ፡ መነሾ ፡ ስለሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ጊዜአዊ ፡ ከሆነ ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ የተሻለ ፡ አስተያየት ፡ ለመውሰድ ፡ አያስችልም ። ባለርስት ፡ መሆን ፡ በአገሩ ፡ ልማድ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ መሆኑ ፡ ከገጠር ፡ ኑሮ ፡ ይልቅ ፡ የከተማ ፡ ኑሮ ፡ በፍጥነት ፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሔድ ፡ የሥራ ፡ እጦት ፡ መፈጠሩ ፤ እንዲሁም ፡ ድህነት ፤ በንብረት ፡ ላይ ፡ ለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ መነሾ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ ግልፍተኞች ፡ ሰዎች ፡ ክብራቸውንና ፡ አቋማቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ያላቸው ፡ የጠነከረ ፡ ፍላጎት ፤ በብዛት ፡ ለሚፈጸሙት ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማድረስ ፡ ወንጀሎች ፡ መነሾ ፡ ከሆኑት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ። ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ በማስፈራራት ፡ ምክንያትን ፡ የተመረኰዘ ፡ ቅንጅት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የወንጀል ፡ አሠራር ፡ አመጣ

27. በልዩ ፡ ልዩ ፡ የወንጀል ፡ ዐይነቶች ፡ መሠረት ፡ ለአሥራ ፡ ሁለት ፡ ተከፍሎ (ተመድቦ) ፡ በተለይ ፡ ይተዳደር ፡ ከነበረው ፡ ከኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በስተቀር ፡ ለሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ የስታቲስቲክስ ፡ መግለጫ ፡ ተሰጥቶአል ። ወንጀል ፡ ሆነው ፡ በፍርድ ፡ ከተገኙት ፡ በመቶ ፡ ሠላሳው ፡ ልዩ ፡ ያልሆኑ ፡ ማንኛውም ፡ ናቸው ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በእስታቲስቲኩ ፡ ውስጥ ፡ ስሕተት ፡ ሞልቷል ። በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ (አውቆ) ሰው ፡ የመግደል ፡ ወንጀል ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ እንደነበረ ፡ ተገልጿል ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቤት ፡ ሰርሰራ ፡ ወንጀልነቱ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ያልተገለጸ ፡ ቢሆን፤ ይሆን ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመዋል ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ቁጥርም ፡ ተመዝግቧል ፤ ተከሳሹ ፡ በቸልተኝነት ፡ ሰው ፡ መግደሉ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ሰው ፡ መጕዳቱ ፡ በእርግጥ ፡ በቸልተኝነት ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ በፖሊስ ፡ ሪፖርት ፡ ይገለጻል ።

ጥና ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ስነፍጥረት ፡ ጥናት ፡ እንዲሁም ፡ የሳይኮሎጂ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። [28]

በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሱ ፡ ወንጀለኞችን ፡ በማስተናገድ ፡ ረገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ ለማድረግ ፡ ያስችላል ። በተጨማሪም ፡ ዳኛው ፡ በተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ ሲወስን ፡ ለሚያደርገው ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፤ የእያንዳንዱን ፡ ወንጀል ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ የሚያትቱት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ቁጥሮች ፡ ክልል ፡ አበጅተውለታል ። [29] በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ የሚገኘው ፤ ሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅጣትና ፡ የቅጣትን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከቱ ፡ ሰፋፊ ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦችን ፡ ይደነግጋል ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሦስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የቅጣት ፡ ዐይነቶችን ፡ ይወስናል ። እነሱም ፡ መቀጮ ፡ እሥራትና ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ ናቸው ። የመቀጮው ፡ መጠን ፡ የሚወሰነው ፡ የአጥፊውን ፡ ግላዊ ፡ ሁኔታና ፡ የጥፋቱን ፡ መጠን ፡ በመመልከት ፡ ነው (ቁ.፹፰) ። ወንጀለኛው ፡ መቀጮውን ፡ ለመክፈል ፡ እንዲችል ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ፤ ባይከፍል ፡ ግን ፡ መቀጮው ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፣ ባይሆን ፡ ሀብቱን ፡ በመያዝ ፡ ይኸም ፡ ደግሞ ፡ ባይቻል ፡ በእሥራት ፤ ሊለወጥ ፡ ይቻላል (ቁ.፺፩—፺፰) ። የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ በሚካሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የተበደለውንም ፡ ወገን ፡ እንዲካስ ፡ ሕግ ፡ በተጨማሪ ፡ ይወስናል ። (ቁ. ፻ —፻፩) ። [30]

28. ወንጀል ፡ እንዲሠራ ፡ ስለሚአነቃቁት ፡ ምክንያቶች ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ ጠቃሚነት ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ይመስለኛል ፤ ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነቷን ፡ ተቋርጦ ፡ ስለነበረ ፡ ታሪኳና ፡ ማኅበራዊ ፡ ዕድገቷ ፡ ከሌሎች ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

29. የሚከተሉት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫውን ፡ ሕግ ፡ ሰፊነት ፡ የሚያሳዩ ፡ በልዩው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።

ቁ. ፫፻፹፫ ፡ በግዙፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። . . . እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

ቁ. ፭፻፳፭ ፡ በዘመድ ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ። . . . እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ይኸውም ፡ ከአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ የመሻሩ ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀር ፡ ነው ።

ቁ. ፭፻፴፯ ። ስለ ፡ ወንበዴነት ። . . . እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ሆኖም ፤ ዳኛው ፡ ከዚህ ፡ ከተሰጠው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ቅጣቱን ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችል ፡ መመሪያ ፡ ተሰጥቶታል ። ቁ. ፹፯ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ፡ የሚለውንና ፡ ከቁ. ፻፲—፻፳ ፡ ቅጣትን ፡ ስለማቃለልና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማክበድ ፡ የሚውለውን ፡ ተመልከት ።

30. እንዲሁም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከቁ. ፻፶፮-፺፱ ተመልከት ።

ከአሥር ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ የእሥራት ፡ ቅጣት፡ ለጠቅላላው ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቂያና ፡ ለወንጀለኛው ፡ ማረሚያ ፡ እንዲሆን፡ በማለት ፡ ከባድነቱ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነ ፡ ጥፋትን ፡ ለሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ የታቀደ ፡ ነው ፡ (ቁ. ፻፷፭) ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰው፡ እንዲበቃ ፡ ያደርገዋል ፡ ብሎ ፡ካመነ ፡ በእሥራቱ ፡ ፈንታ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ፡ (ቁ.፻፷፮) ። የጽኑ ፡ እሥራት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ከባድ ፡ ወን ጀሎች ፡ በሠሩ ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ የታቀደውም ፡ ተቀጭው ፡ እንዲታረም፡ እንደገና ፡ ለመልካም፡ ሰውነት፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልዩ ፡ መከላከያ ፡ ለመስጠት ፡ ሲሆን ፤ በተለይ ፡ የመጨቆንና ፡ የመጠበቅ ፡ ግብ ፡ አለው። የጽኑ ፡ እሥራት ፡ የጊዜ ፡ ርዝመት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ። በግልጽ ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል (ቁ. ፻፷፯) ። የእሥር ፡ ቤት ፡ ኃላፊዎችና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወንጀለኛው ፡ ጠባይ ፡ የተሻሻለና ፡ ወደፊትም ፡ የፈተና ፡ ጊዜ፡ የተሰጠው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ እየተሻሻለ ፡ እንደሚሄድ ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጡ ፡ ምክንያቶች፡ እንዳሉ ፡ ካመኑ፤ የተፈረደበትን ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሲሦ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ፡ ቀዋሚ ፡ ባል ሆነ ፡ ውሳኔና ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ወንጀለኛው ፡ ሊፈታ ፡ ይቻላል፡ (ቁ. ፻፲፱ እና ፡ ፻፸፯) ።

ከተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ ማንኛቸውም ፡ የወንጀለኛን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ማኅ በራዊ ፡ ኑሮ ፡ መመለስ ፡ የማያራምዱ ፡ ሆነው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢታዩና ፡ የወንጀ ለኛው ፡ ጥፋት ፡ በመቀጮ ፤ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያግድና ፡ አጥፊውን ፡ በአመክሮ ፡ ሊያቆየው ፡ ይችላል (ቁ.፻፺፩ — ፻፺፭) ። ለወንጀለኛው ፡ የሚሰጠው ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ ርዝ መት ፡ በሁለትና ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ የአጠባበቁና፡ የጥሩ ፡ ጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንቦችም ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠ ፡ ቁጥር ፡ መወሰን ፡ አለባ ቸው (ቁ. ፻፺፮ — ፻፺፰) ። ወንጀለኞችን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መልቀቅ ፡ ተግባር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ አልተሠራበትም።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶ ችን ፡ ባይደነግግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዋናዎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ። ከተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ዋናዎቹ ፤ ግርፋት [31] ፡ ተግሣፅ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብትን ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ በሙ ያው ፡ ለመጠቀም ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ መከልከልና ፡ ከጦር ፡ ኃይሎች ፡ ውስጥ ፡ መወገድ ፡ ወይም ፡ የማዕርግ ፡ መዋረድ ፡ ናቸው ። እያንዳንዱን ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት፡

31. እላይ ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፲፱-፳፱ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመል ከቱ ።

የሚወስነው ፡ የጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ ቁጥር ፡ የቅጣቱን ፡ ዓላማና ፡ ቅጣቱ ፡ የሚፈጸምባቸውን ፡ ጥፋቶች ፡ ይደነግጋል (ቁ. ፻፳ — ፳፯) ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ከዋናዎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ጋር ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ "ስለ ፡ ጥንቃቄና ፡ ስለ ፡ አጠባበቅ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች" ፡ የተባሉትን ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ። ወንጀለኛው ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሠራ፡ ለመከልከልና ፡ ሕዝቡን ፡ ለመጠበቅ ፡ የታቀዱ ፡ አንዳንድ ፡ ጠቅላላ ፡ እርምጃዎች ፡ ይገኛሉ ። ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ አመራር ፡ ቃል ፡ መግባት ፡ አደገኛ ፡ መሣሪያዎችን ፡ መያዝ ፡ የሥራን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ ማገድና ፡ ወይም ፡ መውሰድ ፡ ወደ ፡ አንድ፡ አንድ ፡ ቦታዎች ፡ እንዳይሄድ ፡ ወይም ፡ እንዲሄድ ፡ ማስገደድ ፡ መቆጣጠር ፡ እና ፡ አጥፊው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ሲሆንም ፡ ከአገር ፡ ማስወጣት ፡ ይገኙባቸዋል (ቁ. ፻፴፰ — ፰) ።

ወንጀል ፡ እየደጋገሙ ፡ ለሚሠሩ ፡ ወንጀል ፡ የመሥራት ፡ ኃላፊነት ፡ ለሌላቸው ፡ እና ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ሳልደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ሕጉ ፡ ልዩ ፡ እርምጃዎችን ፡ ወስኖአል ። [32] ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ የአመለኛነት ፡ ዝንባሌ ፡ ስለአላቸው ፡ ጠባያቸውን ፡ ባለማረም ፡ በሥራ ፡ ፈትነትና ፡ ባልተገባ ፡ ሁኔታ ፡ በመኖር ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ መሥራትን ፡ እንደ ፡ ሙያ ፡ ሥራቸው፡ በማድረግ ፡ የሚኖሩ ፡ ወንጀለኞች ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ በላይ ፡ የማያስቀጣ ፡ ሌላ ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ሲፈጽሙ ፡ በጽኑ ፡ ግዞት ፡ በተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ እንዲቀጡ ፡ ይደረጋል ። ጽኑ ፡ ግዞት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት፡ ለማያንስ ፡ ወይም ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ ለማይበልጥ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተዘጋጀ ፡ በአንድ ፡ የግዞት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጸማል ። ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የግዞቱ ፡ ፍሬ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይግባል ፡ ብሎ ፡ ሐሳብ ፡ ሲያቀርብ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ግዞተኛውን ፡ በአመክሮ ፡ ሊለቀው ፡ ይችላል (ቁ. ፻፳፰ — ፴፪) ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ አዘውትረው ፡ ወንጀል ፡ የሚፈጽሙ ፡ አጥፊዎች ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በዋናው ፡ የእሥር ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ ለብቻቸው ፡ ቢታሠሩ ፡ በገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ምክንያት ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ አልቻሉም ። ወንጀል ፡ የማድረግ ፡ ኃላፊነት ፡ የሌላቸው ፡ ግን ፡ በተስማሚ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ፡ እንዲታከሙ ፡ አደገኞችም ፡ ካልሆኑ ፡ በተመላላሽነት ፡ እንዲረዱ ፡ ይደረጋሉ ። በልዩ ፡ ቦታ ፡ የሚጠበቁት ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆንም ፡ በየሁለቱ ፡ ዓመት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ እንደገና ፡ ማየት ፡ አለበት ። በልዩ ፡ ቦታ ፡ እንዲጠበቁ፡ የተወሰነበት ፡ ምክንያት ፡ ሲወገድ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የሕክምናው ፡ ጊዜ ፡ እንዲያበቃ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ሰውየው ፡ እንዲለቀቅና ፡ ቢያንስ ፡

32. እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፵፩ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ጋር ፡ የሚሄደውን ፡ ቀናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

ለአንድ ፡ ዓመት ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግ ፡ አለበት (ቁ. ፻፴፫ — ፴፯) ። በአስፈላጊዎቹ ፡ ድርጅቶችና ፡ በእእምሮ ፡ መና ወጽ ፡ ምርመራ ፡ ጥናት ፡ ረገድ ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ ዝግጅቶች ፡ ባለመገኘታቸው ፡ ከፍ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሱት ፡ ውሳኔዎች ፡ በሰፊው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ አልቻሉም ።

የታሠሩ ፡ ወንጀለኞች ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሣዊ ፡ ይቅርታ ፡ ወይም ምሕረት ፡ ሊያገኙ ፡ ይቻላል (ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አን. ፴፭ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፴፱ — ፵)። በንግሥ ፡ በዓላቸውና ፡ በሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ በዓሎች ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ በሰፊውና ፡ በልግስና ፡ መጠቀም ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. (፲፱፻፷፫—፷፬ እ. ኤ. አ.) ፻፳ ፡ ሙሉ ፡ ይቅርታና ፡ ፩ሺ፱፻፷፬ ፡ የቅጣት ፡ ቅነሳ ፡ መደረጉን ፡ የእሥር ፡ ቤቱ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ያሳያል ። [33]

አንዳንድ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ በአውራጃው ፡ አንዳንድ ፡ ዋና ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ በየ ጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በጠቅላላው ፡ በግምት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። [34] በተጨማሪም ፡ ለ፩፻፱ ፡ እሥረኞች ፡ የሚበቃ ፡ የእርሻ ፡ ጣቢያ ፡ በሮቢት ፡ ተቋቁሟል ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ስታቲስቲ ክስ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. ፲፮ሺ፩፻፺፬ ፡ ሰዎች ፡ ታሥረው ፡ ነበር ። የእሥረኞቹ ፡ ብዛት ፡ ከ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. በ፪ሺ፹፬ ፡ ከ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. በ፭ሺ፸፰ ፡ መጨመሩ ፡ ነው ። [35] ፫ሺ፫፻፫ ፡ ሰዎች ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ ፭ሺ፻፸፩ ፡ ሰዎች ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚያንስ ፡ ጊዜ ፡ እሥራት ፡ ሲፈረድባቸው ፡ ዕድሜ ፡ ልካቸውን ፡ እንዲታሠሩ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ፳፺ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ፺ሺ፩፻፶፮ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጣቸው ፡ በመጠባበቅ ፡ ታሥረው ፡ ነበር ።

33. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ (ሪፖ ርት) ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

34. ሆኖም ፡ ኤሪትርያ ፡ ወህኒ ቤቶቿን ፡ እንደቀድሞው ፡ ራስዋ ለብቻዋ ፡ ታስተዳድራለች ።

35. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ዓመታዊ መግለጫ ፡ ከ፲፱፻፶፬ — ፶፯ ፡ ዓ. ም. ።

ከዚህ ፡ በአቆጣጠሩ ፡ ጥቂት ፡ የተለየውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የስታቲ ስቲክስ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ (፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም.) ፡ የተዘጋጀውን ፡ እስታቲስቲካል ፡ አብስትራ ክት ፡ ከገጽ ፡ ፻፶፬-፷፩ ፡ ተመልከት ። የእስረኞቹ ፡ ቁጥር ፡ የበዛው ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ የተሟላ ፡ መግለጫ ፡ በመተላለፉ ፡ ምክንያት ፡ ይሆ ናል ።

በአገሪቱ ፡ ከሚገኙት ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የተራመደው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ነው ። [36] እሥረኞች፡ በጽኑ እሥራት ፡ ሦስት ፡ ንኡስ ፡ ክፍሎችና ፡ በሦስት ፡ ንኡስ ፡ የእሥራት ፡ ክፍሎች ፡ ይመደባሉ ።

ፍርድ ፡ የሚጠባበቁ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ የተፈረደባቸው ፡ ወይም ፡ የሞትን ፡ ቅጣት ፡ የሚጠባበቁ ፡ እሥረኞች ፡ ከተራ ፡ እሥረኞች ፡ ተለይተው ፡ ይታሠራሉ ፤ በእሥር ፡ ቤቱም ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋዮች ፡ አይሆኑም ። የእሥር ፡ ቤቱ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የእሥረኞችን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ማያገኙና ፡ ራሳቸውም ፡ ይኸን ፡ ስለማያዘጋጁ ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ ለማብቃት ፡ የሚደረገው ፡ ቅንጅት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ።

የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት፡ ፕሮግራሞች ፤ በመጻጻፍ፡ የሚጠኑ ፡ ኮርሶችና፡ ያልተስፋፉ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አገልግሎት ፡ እሥረኞች ፡ እንዲያገኙ ፡ ተደርጓል ። እሥረኞቹ ፡ ፺፰ ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑት ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ አይችሉም ፤ [37] ፡ ከእሥራቱ ፡ ሲፈቱ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ በሚጠቅሟቸው ፡ የሙያ ፡ ትምህርት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻል በት ፡ በተለይም ፡ በርሻ ፡ በከብት ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራሞች ፡ ወጥተዋል ። የሚያሳዝነው ፡ ግን ፡ ገንዘብ የማግኛ ፡ እቅዶች ፡ ገና ፡ ባለመውጣታቸው ፡ እሥረኞች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ እቅድ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በተረቀቀው ፡ የእሥር ፡ ቤት ፡ አዋጅ ፡ ታስቦበታል ። ረቂቁ ፡ በሥራ ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ በሦስት ፡ የሒሳብ ፡ መደብ ፡ ማለት ፡ በየ

36. አብዛኛው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈው ፡ ነገር ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተገኘና ፡ እኔም ፡ የአዲስ ፡ አበባን ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተመላልሼ ፡ በመጐብኘት ፡ የተረዳሁት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከሪንት፡ ፕሮጀክትስ ፡ ኤን ዘ ፕሪቬንሽን ፡ ኮንትሮል ፡ ኤንድ ፡ ትሪትመንት ፡ ኦቭ ፡ ክራይም ፡ ኤንድ፡ ዲሊን ፡ ኩዌንሲ፡ ( ወንጀልንና፡ የወጣቶችን፡ ወሮበላነትነት) (ሥራ፡ ፈትነት) ፡ ለማቆምና፡ ለማስቀረት፡ በአሁኑ፡ ጊዜ ፡ ሊወሰድ ፡ የታቀደ ፡ እርምጃ) ፡ በሚል ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ከገጽ ፡ ፮—፱ ፡ (፲፱፻፭፫ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) አቶ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ተሰፋዬ ፡ "ኮሬክሽን፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ" ፡ (በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኞች ፡ እርማት ፡ መታረም) " በሚል ፡አርእስት " ፡ የጻፉትን ፡ ተመልከት ።

37. አቶ ፡ ሜንያለው ፡ ተሾመ ፡ "ሚሞራንደም ፡ ኦን ፡ ዘ ኢምፕሩቭመንት ፡ ኦቭ ፡ ፕሪዘን፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ (ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻል ፡ ማስታወሻ) ፡ በሚል ፡ ያቀረቡትን ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

ጊዜው ፡ የሚሠራበት ፡ ሒሳብ ፡ በሚጠራቀም ፡ ሒሳብና ፡ ለካሣ ፡ በሚከፈል ፡ ሒሳብ ፤ በመመደብ ፡ ይከፈፍለዋል ። [38]

የገንዘብ ፡ እጦት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ እንኳን ፡ ያሉትን ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ ባሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንዲወድቁ ፡ አድርጓቸዋል ። በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ በቂ፡ሠራተኞች ፡ ለመቅጠርና ፡ ለማሠልጠን ፡ የማይቻል ፡ ሆኗል ። መዝናናት ፤ ጤንነትና ሕክምና ፡ የሚበፋፋባቸው ፡ አቅዋሞች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። ከእሥራትም፡በኋላ፡ ለሚደረገው ፡ ጥንቃቄ ፡ አስፈላጊው ፡ ፕሮግራም ፡ ገና ፡ አልተዘጋጀም ። እሥረኞች ፡ እንደሚማረሩና ፡ መታሠራቸውም ፡ በፍርድ ፡ መጓደል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ እንዳላቸው ፡ ይነገራል ። [39] የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያላቸው ፡ መሰናዶ ፡ የባሰውን ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፤ እሥረኞቹ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚሰጣቸውም ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። አሳፊነታቸውን ፡ የተረዱት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦች ፡ ፍሬ ፡ በማያስገኝ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ከተፈለገ ፤ ጥሩ ፡ የእሥር ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ማስፈለጉንና ፡ በጥንቃቄ ፡ የማቀድን ፡ ጠቃሚነት ፡ ስለተገነዘቡ ፤ ይህን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ጀምረዋል ።

## መ/ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወንጀለኞች ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ስለደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ቁጥራቸው ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ መግለጫዎች ፡ ስለሚገኙና ፡ የተሟላ ፡ ጥናት ፡ በጉዳዩ ፡ ስላልተደረገ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ጥፋቶች ፡ የሚሰጡት ፡ ሐተታዎች ፡ ዘለቄታ ፡ ጊዜአዊ፡ከመሆን ፡ አያልፍም ። [40] በአዲስ ፡ አበባ ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ የወጣቶች ፡ ማቆያና ፡

38. ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ የፓርላማ ፡ ስብሰባ ፡ ጊዜ ፡ ለፓርላማው ፡ እንዲቀርብ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ በብዛት ፡ የሚያወሳው ፡ ስለእስረኞች ፡ ጥበቃ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ቢታሰብም ፤ እስከ ፡ አሁን ፡ ስለ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ምንም ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ የሕጉ ፡ መውጣት ፡ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቅጥ ፡ ያለው ፡ አስተዳደር ፡ እንዲኖራቸውና ፡ አስተዳደሩም ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ።

39. ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአቶ ፡ ሚንያለው ፡ ተኾመ ፡ ጽሑፍ ፡ ገጽ ፡ ፪ ፡ ተመልከት ።

40. ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የተላኩት፡ አማካሪ፡ ክሂ. ራይሌ ፤ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ወጣት ፡ (የአካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ) አጥፊዎች (ወንጀለኞች) ፡ በጣም ፡ የተሟላ ፡ ጥናት (ምርምር) የመጨረሻ ፡ መግለጫ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ ቀርቦለታል ። ሌላ ፡ ሁለት ፡ አጫጭር ፡ ጥናቶች ፡ በሚከተሉት ፡ ገና ፡ ያልታተሙ ፡ መግለጫዎች ፡ ውስጥ ፡ አሉ ፤ ከሂ . ሮስ፡ የተጻፈው ፡ "ጁቨናይል ፡ ዴሊንኩዌን ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች" እና ፡ ከወይንእሸት ፡ በሻህ ፡ ውረድ ፡ የተጻፈው ፡ "ሳም ፡ ሔቨ ፡ ዘ. ኮዝስ ፡ አንድ፡ ኮንትሪቢዩቲንግ ፡ ፋክተርስ ፡ ቱ፡ ዚ ፡ ሚኪንግ ፡ ኦቭ፡ ጆቨናይል ፡ ዴሊንኩዌንሲ ፡ ኤንድ ፡ ፕሮስቲቲዩሽን (ወጣት ፡ አጥፊዎችና ፡ ሴት ፡ አዳሪዎችን ፡ ስለሚፈጥሩ ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያቶችና ፡ እንሱን ለመፍጠር ፡ ስለሚረዱ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች) (፲፱፻፷፮ ፡ እ.ኤ.አ.) ። እንዲሁም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአቶ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ተሰፋዬን ፡ ጽሑፍ ፡ (ከገጽ ፡ ፱—፲፩) ፡ ተመልከት ።

ማሠልጠኛ ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ ፋይሎች ፣ ውስጥ ፣ የሚገኙት ፣ የየጉዳዩ ፣ ታሪክ ፣ ጽሑፎች ፣ ሲመረመሩ ፣ ግን ፤ አካለ ፣ መጠን ፣ ያላደረሱ ፣ ወጣቶች ፣ ስለሚፈጽሙአቸው ፣ ወንጀሎች ፣ አዝማሚያ ፣ ጥቂት ፣ ፍንጭ ፣ ይሰጣል ። ከፍ ፣ ብሎ ፣ ከተጠቀሰው ፣ መረጃ ፣ ሊወጣጡ ፣ የሚችሉት ፣ ዋና ፣ ዋና ፣ ማጠቃለያ ፣ ሐሳቦች፣በቅርቡ ፣ ለሕዝባዊ ፣ ኑሮ ፣ እድገት ፣ ሚኒስቴር ፣ በቀረበው ፣ መግለጫ ፣ ውስጥ ፣ በአጭር ፣ ሠፍረዋል ። [41] አብዛኛውን፣ ጊዜ ፣ አካለ፣ መጠን ፣ ያልደረሱ፣ አጥፊዎች ፣ የሚፈጽሟቸው ፣ የወንጀሎች ፣ ብዛት ፣ የሚገኙት ፣ በጥቂት ፣ ታላላቅ ፣ ከተሞች፣ ውስጥ ፣ ነው ። እነዚህም ፣ ጥፋቶች ፣ ለጊዜው ፣ አነስተኛ ፣ ቢሆኑም ፣ ቁጥራቸው፣ እያደገ ፣ በመሔድ ፣ ላይ ፣ ነው ። [42] በጣም ፣ አስፈላጊ ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ በሥራ ፈትነት ፣ ወንጀል ፣ ረገድ ፣ እርምጃ ፣ እንዳይወሰድ ፣ ባለሥልጣኖቹ ፣ ቢወስኑም ፣ ከሁሉ ፣ ይበልጥ ፣ የሚፈጸሙት ፣ ጥፋቶች ፣ ሥራ ፣ ፈትነትና ፣ ቀላል ፣ ስርቆት ፣ ናቸው ። [43] በአሥራ ፣ ሁለትና ፣ በአሥራ ፣ ስድስት ፣ ዓመት ፣ መካከል ፣ ያለው የዕድሜ ፣ ደረጃ ፣ አብዛኛውን ፣ የወጣት ፣ ወንዶች ፣ አጥፊዎች ፣ ክፍል ፣ የያዘ ፣ ነው ። ከነዚህም ፣ አጥፊዎች፣ መካከል፣ አባትና ፣ እናታቸው ፣ አብረው ፣ ከሚኖሩ በት ፣ ቤተሰብ ፣ ውስጥ ፣ የሚመጡት ፣ አሥራ ፣ ስምንት ፣ በመቶ፣ ብቻ ፣ ናቸው። ። እንዲሁም ፣ የአበል ፣ አነስተኛነት ፣ መሀይምነትና ፣ በሥራ ፣ እጦት ፣ ምክንያት ፣ ሥራ ፣ ፈት ፣ መሆን ፣ በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ወጣት ፣ አጥፊዎች ፣ ከሚፈጽሙአቸው ፣ ወንጀሎች ፣ ጋር ፣ የተያያዙ ፣ የወል ፣ ምክንያቶች ፣ ናቸው ።

አካለ ፣ መጠን ፣ ባላደረሱ ፣ ወጣቶች ፣ ስለሚፈጸሙት ፣ ወንጀሎች ፣ መነሾ ፣ ማተት ፣ ከዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ክልል ፣ ውጭ ፣ ቢሆንም ፣ መመርመር፣ ስለሚገባቸው፣ ጥቂት ፣ ጠቃሚ ፣ ሐሳብ ፣ ማቅረብ ፣ ተገቢ ፣ ይሆናል ። በፍጥነት ፣ እየጨመረ ፣ የሚሔደው ፣ የባላገሩ ፣ ሕዝብ ፣ ወደ ፣ ከተማ ፣ በተለይም ፣ ወደ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ መግባትና ፣ ይኸም ፣ ያስከተለው ፣ ከቤተሰብ ፣ አብዛኛውንም ፣ ጊዜ ፣ ከቤተ ፣ ክር

41. የተጠቀሰውን ፣ የሬዳሌ ፣ ጽሑፍ ፣ ገጽ ፣ ፰ ፣ ፻፸—፻፸፮ ።

42. ስለወጣት ፣ ወንጀለኞች ፣ ብዛት ፣ ትክክለኛ ፣ የታወቀ ፣ ቁጥር ፣ የለም ፤ ከአዲስ ፣ አበባ ፣ ከድሬዳዋና ፣ ከአሥመራ ፣ ውጭ ፣ ብዙ ፣ ወጣት ፣ አጥፊዎች ፣ የሉም ። ቢኖሩም ፣ ጉዳያቸው ፣ በቀላሉ፣ በይፋ ፣ ሳይሆን ፣ በፖሊስ ፣ ይወሰናል ። የተጠቀሰውን ፣ የሬይሌ ፣ ጽሑፍ ፣ ከገጽ ፣ ፻፮—፻፲ ፣ ተመልከት ።

43. በማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ላይ ፣ ጉዳት ፣ የሚያደርሱን ፣ ስለመከላከል (የማኅበራዊ ፣ እድጋ ፣ መከላከያ) ፣ እ. ኤ. አ. —አገስት ፣ ፲፱፻፷፱ ፣ በሞንሮቪያ ፣ ለተሰበሰበው ፣ ጉባኤ ፣ ኢትዮጵያ ፣ "ዘካንትሪ ፣ ስቴትሜንት ፣ አቭ ፣ ኢትዮጵያ ፣ (የኢትዮጵያ ፣ ማስረጃ) " በሚል ፣ አርእስት ፣ ያቀረበችው ፣ ጽሑፍ ፣ በገጽ ፣ ፪ ፣ ላይ ፣ "ከመቶ ፣ ውስጥ ፣ ፷፰ ፣ ልጆች ፣ የሚከሰሱ ፣ በጥቃቅን ፣ ስርቆትና ፣ ወሮበልነት ፣ ነው ፣ " ይላል ። አዲስ ፣ በተወሰደው ፣ እርምጃ፣ ምክንያት ፣ በወሮበልነት ፣ የሚያዙት ፣ ብዛት ፣ ተቀንሶ ፣ ከመቶ ፣ ውስጥ ፣ አምሳ ፣ የነበረው ፣ ከመቶ ፣ ውስጥ ፣ ሁለት ፣ ሆኗል ። የተጠቀሰውን ፣ የሬደሌ ፣ ጽሑፍ ፣ ገጽ ፣ ፱ ፣ ተመልከት ።

ስቲያን ፡ መለየትና ፡ መራቅ ፡ ከምዕራባውያን ፡ የትምህርትና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ሐሳቦች ፡ መምጣት ፡ ጋር ፡ ተደርቦ ፡ በተለየ ፡ ወጣቶችን ፡ ለሚማርከው ፡ የሥርዓት ፡ መዘበራረቅ ፡ መነሾ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ከጥንት ፡ የቆየውን ፡ ሥልጣን ፡ አቋምና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ መፈራረስ ፡ መርቶታል ፤ ይኸም ፡ በተራው ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱ ፡ አጥፊዎች ፡ ሊፈጽሙ ፡ የሚችሉትን ፡ ወንጀል አበርክቶታል ። እነዚህ ፡ ለውጦች ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ አቅዋም ፡ ጥልቀት ፡ ባለው ፡ ሊኳኋን ፡ ነክተዋል ።

ይልቁንም ፡ የቤተ ፡ ሰብ፡ አቅዋም ፡ ጥንቱኑ ፡ ባልሆነበት [44] ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚፈጸም ፡ የወጣቶች ፡ ወንጀል ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ የሳይኮሎጂ ፡ ሁናቴ ፡ ሥሩን ፡ የሰደደ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ድኅነት ፡ የሥራ ፡ እጦትና ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ መወሰን ፡ በወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ለሚፈጸሙት ፡ ወንጀሎች ፡ በተለይም ፡ አዘውትሮ ፡ ለሚፈጸመው ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተጨማሪ ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልጆች ፡ የሚሠሩት ፡ የወንጀሎች ፡ ቁጥር፡ አነስተኛ፡ የሆነበት ፡ ከፊል ፡ ምክንያት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ ጥንት ፡ በቆዩት ፡ ድርጅቶች ፡ ብርታት ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። በልጆች ፡ የሚፈጸመውን ፡ ወንጀል ፡ ማስወገጃና ፡ አጥፊዎቹን ፡ ማስተናገጃ ፡ ለሚሆን ፡ ለተሟላና ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ለሚያስገኝ ፡ አቅድ ፡ ትክክለኛውን ፡ መሥመር ፡ ለመዘርጋት ፡ እንዲቻል ፡ ይኸን ጊዜአዊ ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ለመደገፍም ፡ ሆነ ፡ ለመቃወም ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አስተያየቶችን ፡ ለማቅረብ ፡ ጥልቅ ፡ ጥናትን ፡ የተመረከዘ ፡ ምርምር ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የወጣው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕግ ፡ "የ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ ዘዋሪዎችና ፡ስለ ወሮበሎች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ" ፡ ነበር ። [45] አዋጁ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፲፰ ፡ ዓመት፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ ደንበኛ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ሳይኖራቸው እየዞሩ ፡ ቢገኙ ። [46] በልዩ ፡ ቦታ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ያውጃል ። የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም.

44. ኡለንዶርፍ ፡ የጻፈውን ፡ ዘኢትዮጵያንስ ፡ (ኢትዮጵያን) (፲፱፷፰ ፡ እ. ኤ. አ.) ገጽ ፡ ፻፷፰ ፡ እና ፡ ሊፕስኪ ፡ የጻፈውን ፡ —ኢትዮጵያ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ (፲፱፻፷፪ ፡ እ. ኤ. አ.) ገጽ ፡ ፹ ፡ ተመልከት ።

45. ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፹፱ ። የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ትንሽ ፡ ይጠቅሳል ፤ ቁ.፷፩ ፡ እና ፡ ፻፺ ፡ ተመልከት ።

46. ወጣቱ ፡ አጥፊ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ ሲሠራ ፤ በአንሱ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ ለእናት ፡ አባቱ ፡ ይሰጣል ፤ ክፍል ፡ ፰ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ አዋጅ ፡ ሽሮታል ።[47]

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት[48] ፡ ያልሞላ ፡ ሕፃናት ፡ ወንጀል ፡ ቢሠሩ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳላቸው ፡ ሆነው ፡ አይቈጠሩም ። እንዲህ ፡ ባሉት ፡ ሕፃናት ፡ የሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ በቤተሰብ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ በሚመለከተው ፡ ሞግዚት ፡ አስፈላጊው ፡ እርምጃ ፡ ይወሰዳል (ቍ. ፶፪) ። ዕድሜያቸው፡ በዘጠኝና ፡ በ፲፭ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ "አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች፡ ወይም ፡ ወጣቶች" ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፤ ለአዋቂዎች ፡ ጥፋተኞች ፡ በተመለከቱት ፡ በደንበኞቹ ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረት ፡ አይቀጡም ( ቍ. ፶፫ )።

ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚወሰነው ፡ በአጥፊው ፡ ወጣት ፡ ዕድሜ ፡ በጠባዩ ፡ በአእምሮውና ፡ በግብረ ፡ ገብነቱ ፡ የደረሳበትን ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ እንደዚሁም ፡ የሚፈጸሙበት ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዓላማ፡በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ለማሳደግ ፡ እንዲሆን ፡ በማሰብ ፡ መመራት ፡ አለበት (ቍ. ፶፭) ።

47. የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ "በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብና ፡ ለርሱ ፡ ማሻሻያ ፡ ሆነው ፡ የወጡት ፡ አዋጆችን ፡ ሁሉ ፡ ጭምር" በግልጽ፡ ይሽራቸዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሕግ ፡ ቍ.፫ ፡ "ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሚሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ደንቦችና ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው" ቢል ፤ ስለዘዋሪዎችና፡ ወሮበሎች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ወንጀል ፡ ጠቀስ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ከመሆን ፡ ይልቅ ፡ የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ለማሻሻል ፡ የወጣ ፡ ይመስላል ። አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥራፈትነትን ፡ የሚመለከት ፡ ቁጥር ፡ ስለ ፡ አለው ፤ (ቍ. ፭፻፷፭ ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት) ስለዚህ ፡ አጋጉዎች ፤ ለምንም ፡ እንኳ ፡ በግልጽ፡ ባይጽፉት ፡ ስለ ፡ ሥራ ፈትነት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ለመሻር ፡ የፈለጉ ፡ ይመስላል ። ስለዘዋሪዎችና ፡ ወረበሎች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ መሻሩን ፡ የሚያመለክተውን ፤ በፓብሊክ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ ኢንስቲትዩት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኮንሶሊዴትድ ፡ ሎውስ ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕጎችን ፡ በጠቅላላ፡ የሚያሳይ) የሚለውን ፡ ተመልከት ። ሆኖም ፤ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ችሎት ፡ ሁለት ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን ፡ስለ፡ ዘዋሪዎችና፡ ወረበሎች፡በወጣው፡አዋጅ፡ሕግ፡ ቍ.፰ ፡ መሠረት ፡ ፈርዶባቸዋል ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ችሎት ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቍ. ፩፻፭፲/፶፫ ፡ ዓ.ም. ፤ ይኸን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሎውንስታይን ፡ በ፲፱፻፷፭ ፡ እ. ኤ. አ. ፡ በጻፈው ፡ —ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ስተዲ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ፔናል፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማጥናት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጽሑፎች ) በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፱—፲ ፤ ታገኘዋለህ ።

48. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አርቃቂ ፡ በፈረንሣይኛ ፡ የጻፈው ፡ ረቂቅ ፡ "ዐሥር" ዓመት፡ ይላል ፤ — " ሌ ዲስፖዚሲዮ፡ ዲ ፡ ፕሬዛንት፡ ኮድ፡ ን፡ ሶንት ፡ አፕሊካብልዝ ፡ አዝ፡ አንፋ ፡ ን ፡ አያ፡ ፓዝ ፡ አቴያ ፡ ሌ፡ አዥ፡ ዴ ፡ ዲስ ፡ አንሬቮሉ።" ስለወጣት፡ (አካለ ፡ መጠን፡ ያላደረሱ) አጥፊዎች ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በተጠቀሰው ፡ ዕድሜ ፡ ሁሉ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ የአተረጓጐም ፡ ስሕተት፡ ተደርጓል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ አንዱን ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ከነሱም ፡ በጣም ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ወደሕክምና ፡ ድርጅቶች ፡ መግባት ፤ በዘመዶች ፤ ባሳዳጊ ፣ በማደጎ ፡ ልጅነት ፡ በሚቀበለው ፡ ቤት ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የርኅራኄ ፡ ተግባር ፡ በሚፈጸም ፡ ድርጅት ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ በበጎ ፡ አስተዳደግና ፡ በትምህርት ፡ መጠበቅ ፡ ተግሣጽ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ናቸው (ቁ. ፻፷፩ — ፷፱) ። ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመቀጮ ፡ ክፍያ ፤ የአለንጋ ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የተፈጸመው ፡ በደል ፡ ለአሥር ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ከሆነና ፡ አጥፊው ፡ የማይታረም ፡ መስሎ ፡ ከታየ ፡ እንዲያውም ፡ እሥራት ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል (ቁ. ፻፸ — ፸፫) ።

ለማሳከም ፡ ወይም ፡ በተጠባባቂነት ፡ ለማስተማር ፡ የተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ የሚቋረጡት ፡ የሕክምናው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የጥበቃ፡ ተቈጣጣሪው፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ አለበለዚያም ፡ የአጥፊው ፡ ወጣት ፡ ዕድሜ ፡ አሥራ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሲሞላ ፡ ነው ። ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ድርጅቶች ፡ የተላኩ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ግን ፡ እዚያው ፡ የሚቆዩት ፡ ከአንድ፡ዓመት ለማያንስ ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ያጥፊው ፡ ዕድሜ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ከሞላ ፡ በኋላ ፡ እሥራቱ ፡ የሚቀጥለው ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው (ቁ. ፻፷፯) ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለፈተና ፡ በአመክሮ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ሕጉ ፡ ያዛል (ቁ. ፻፷፯) ። ነገር ፡ ግን ፡ ቅጣቱን ፡ አሳማጆ ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት፡ በኩል፡ የተደራጀ ፡ ነገር ፡ በመታጣቱ፡ይኸ ፡ ውሳኔ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ አይቻልም ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተጨማሪ ፡ ዕድሚያቸው ፡ በ፲፭ ፡ እና ፡ በ፲፰ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ለሆነ ፡ ጥፋተኞች ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ አበጅቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደንበኞቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ሊፈጸሙ ፡ ቢቻል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጣት ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ጥፋቱን ፡ የሚያቃልሉ፡ ልዩ፡ ምክንያቶች፡ ሲመለከትና፡ ቅጣቱን፡ ሊያቃልል ፡ ይችላል (ቁ. ፺፯) ።

ከ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ከልጁ ፡ መልካም ፡ አጠባበቅ ይልቅ ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ወደሚታይበት ፡ ለአዋቂ ፡ አጥፊዎች ፡ ወደ ፡ ተዘጋጁ ፡ ተራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይቀርቡ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ. ም. በአዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ በወጣቶች ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ክስ ፡ ለመስማት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ያሉበት ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቋቋመ ። ይኸ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ፡ እንዲያስችል ፡ ልዩ ፡ የወጣቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ እስከ ፡ ተቋቋመበት ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም፡ ድረስ ፡ አገለገለ ። የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ የማኅበራዊ ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ ዲሬክተር ፡ ለወጣቶች ፡ በተቋቋመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡትን ፡

ክሶች ፣ ለመስማት ፣ የወረዳ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ ሁኖ ፣ ተሹሟል ። በጠቅላይ ፣ ግዛቶች ፣ ውስጥ ፣ አሁንም ፣ ቢሆን ፣ ወጣቶች ፣ አጥፊዎች ፣ የሚቀርቡት ፣ ለዓዋቂ አጥፊዎች ፣ በተቋቋሙት ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ነው ።

የ፲፱፻፶፬ ፣ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ወጣት ፣ አጥ ፊዎችን ፣ በሚመለከቱ ፣ ጉዳዮች ፣ በኩል ፣ ልዩ ፣ የአቀጣጥ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ ደን ቦችን ፣ ያዛል (ቁ. ፻፸፩ —፻፹) ። እነዚህ ፣ ደንቦች ፣ የተፈጸመው ፣ ወንጀል ፣ ከአ ሥር ፣ ዓመት ፣ ለሚበልጥ ፣ ጊዜ ፣ በጽኑ ፣ እሥራት ፣ ወይም ፣ በሞት ፣ የሚያስቀጣ ካልሆነ ፣ ሕግ ፣ አስከባሪው ፣ የክስ ፣ ማመልከቻውን ፣ አዘጋጅቶ ፣ ሳይቀርብ፣ጉዳዩ እችሎት ፣ ክፍል ፣ ሳይሆን ፣ ሌላ ፣ ክፍል ፣ አለ ፣ ብዙ ፣ ድግድግ ( አለ ፣ ፎርማ ሊቲ) ፣ እንዲሰማ ፣ ይደነግጋሉ ። አቤቱታው ፣ ለተከሳሹ ፣ ከተነበበለት ፣ በኋላ ፣ ጥፋቱን ፣ ቢያምን ፣ ፍርድ ፣ ወዲያውኑ ፣ ሊሰጥ ፣ ይቻላል ። ጥፋቱን ፣ ቢክድ፣ግን፣ ለወጣቶች ፣ በተሾመው ፣ ዳኛና ፣ በሚከላከልለት ፣ ጠበቃ ፣ ወይም ፣ አሳዳጊ ፣ ምስ ክሮች ፣ እየተጠየቁ ፣ ጉዳዩ ፣ ይደመጣል ። ዳኛው ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ከተቋቋሙት፣መሠረት፣ ሐሳቦች፣ሳይዛባ፣የአጥፊውን፣ቅጣት፣ ለመወሰን፣ እንዲችል፣ ቅጣቱ ፣ ታግዶ ፣ የፈተና ፣ ጊዜ ፣ ስለሚሰጥ ፣ አኳኋን ፣ ከፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጋር ፣ ተባ ብረው ፣ ከሚሠሩት ፣ ከሁለቱ ፣ የጠባይ ፣ ማሻሻል ፣ ጥበቃ ፣ ዘበኞች ፣ በአንዱ ፣ ጽሑፍ ፣ መግለጫ ፣ ይዘጋጃል ።[49] ልጃገረዶች ፣ የሚጠበቁበት ፣ ቤት ፣ ገና ፣ ስላልተዘጋጀላቸው ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ ወላጆቻቸው ፣ ወይም ፣ ወደ ፣ አሳዳጊ ዎቻቸው ፣ ይመለሳሉ ፤ ወይም ፣ አንዳንድ ፣ ልዩ ፣ ሁኔታዎች ፣ በተገኙ ፣ ጊዜ ፣ ይታሠራሉ ።[50]

በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ወጣቶች ፣ አጥፊዎችን ፣ እንደገና ፣ ለመልካም ፣ ሰው ነት ፣ እንዲበቁ ፣ ለማድረግ ፣ የሚረዳ ፣ ድርጅት ፣ በ፲፱፻፴፰ ፣ ዓ. ም. በአዲስ ፣ አበባ ፣ የተቋቋመው ፣ የጠባይ ፣ ማረሚያ ፣ የወጣቶች፣ ማቆያና ፣ ማሠልጠኛ ፣ ትም ህርት፣ ቤት፣ ብቻ፣ ነው ።[51] እስከ፣ ግንቦት፣ ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ. ም. ድረስ፣ ትምህርት ፣

49. በ፲፱፻፶፰ ፣ ዓ. ም. የወጣት ፣ ( አካለመጠን ፣ ያላደረሱ ) ፣ ወንጀለኞች ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ ከአጥፊዎቹ ፣ በሙሉ ፣ ፺፰.፰ን ፣ ወደ ፣ ጠባይ ፣ ማረሚያ ፣ የወጣቶች ፣ ማቆያና ፣ ማሠልጠኛ ፣ ትምህርት ፣ ቤት እንዲላኩ ፤ በሙሉ ፣ ፻፫ ፣ ቅጣቱ ፣ ሳይፈጸምባቸው ፣ የፈተና ፣ ጊዜ ፣ እንዲሰጣ ቸው፤ በሙሉ ፣ ፴፰ ፣ ደግሞ ፣ ወደቤተሰቦቻቸው ፣ እንዲመለሱ ፣ ፈርዱዋል ። ከላይ ፣ የተጠቀ ሰው ፣ የራይሌ ፣ ጽሑፍ ፣ ገጽ ፣ ፩ ።

50. የወጣት (አካለ ፣ መጠንያላደረሱ) አጥፊዎች ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ የሆኑት ፣ አቶ ፣ አንዳርጋ ቸው ፣ ተሰፋዬ ፣ እ. ኤ. አ. ዲሰምበር ፣ ፲፯ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፷፬ ፣ ባደረግንላቸው ፣ ጥያቄ ፣ መሠረት፤ ለልጅ ፣ አገረዶች ፣ የሚሆን ፣ ድርጅት ፣ ካለመኖሩም ፣ በላይ ፤ ዋናው ፣ ችግር ፣ የአገልግሎት ፣ መሣሪያዎች ፣ አለመኖርና ፤ በጠቅላይ ፣ ግዛቶች ፣ ፖሊስና ፣ በወጣት ፣ አጥፊዎች ፍርድ ፣ ቤት ፣ መካከል ፣ ኅብረት ፣ አለመኖሩ ፣ ነው ፣ ሲሉ ፣ ገልጸዋል ።

51. በየጠቅላይ ፣ ግዛቱ ፣ ያሉ ፣ ወጣት ፣ ወንጀለኞች ፣ በእሥር ፣ ቤቶች ፣ ልዩ ፣ ቦታ ፣ ካለ ፤ የሚታ ሠሩ ፣ ከሌሎቹ ፣ እሥረኞች ፣ ተለይተው ፣ ነው ።

ቤቱ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሥር ፡ ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ እየተስፋፋ ፡ በሚሄደው ፡ የትምህርትና ፡ አጥፊውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ ማብቃት ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፤ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥር ፡ ወዳለው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ክፍል ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ተዛወረ ።

ድርጅቱ ፡ ሲገቡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ በዘጠኝና ፡ በአሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ሁኖ ፡ ለሚታሠሩ ፡ ወይም ፡ ለሚታረሙ ፡ አንድመቶ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ በቂ ፡ ሥፍራ ፡ አለው ።[52] ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ የሚያኪያሂዱት ፡ አንድ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሁለት ፡ የጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኞችና ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካይነት ፡ የአንደኛን ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፤ ከአነስተኛ ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፤ በጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኞች ፡ ከሚሰጠው ፡ ጥቂት ፡ ሕክምናና ፡ የችግር ፡ ውይይት ፡ በቀር ፡ የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ በመታጣታቸው ፡ ልጆቹ ፡ ምንም ፡ መምሪያና ፡ ምክር ፡ አያገኙም ። የትምህርት ቤቱ ፡ በድርጅቱና ፡ በአቅዱ ፡ ልል ፡ የሆነ ፡ በመዛሪያዎችና ፡ በቤት ፡ ሁኔታ ፡ ረገድ ደህየት ፡ ያለ ፤ በቂ ፡ ሠራተኞች ፡ የሌሉት ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። እስካሁን ፡ ድረስ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ሲወጡ ፡ ለወጣቶች ፡ አጥፊዎች ፡ የሚደረግ ፡ ጥንቃቄ ፡ ወይም ፡ መከታተል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የለም[53] ! ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለባቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አጥፊውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ የማብቃትን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦችን ፡ ይደግፋሉ ፤ በዚህም ፡ ረገድ ፡ ደህና ፡ በመራመድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ እንደገና ፡ ለማደርጀትና ፡ ለማስፋፋት ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ አቅድ ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ተዘጋጅቷል ፤ ሥራ ፡ ላይ ፡ ቶሎ ፡ እንደሚውልም ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለ ።[54]

በወጣቶች ፡ የሚደረገውን ፡ ወንጀልና ፡ ዘዋሪነት ፡ ለመቆጣጠር ፤ እንደዚህ ያሉትንም ፡ ወጣቶች ፡ ለማኅበራዊ ኑሮ ፡ ጠቃሚ ፡ አባሎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመርዳት የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቁ ፡ ለማድረግ ፡ ጥረት ፡ ያደርጋል ፡ የሚል ፡ መሠረት ፡ ሐሳብ ፡ በሁ

52. በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፻፴፰ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ከእነዚሁ ፡ ውስጥ ፻፳፯ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ የገቡ ፡ ሲሆኑ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲቆዩ ፡ የተላኩ ፡ ነበሩ ። ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የራደሉ ፡ ጽሑፍ ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ።

53. የተጠቀሰውን ፡ የራድሉ ፡ ጽሑፍንና ፡ ሲንግ ፡ "አዲስ ፡ አበባ ፡ ሆም ፎር ፡ ጁቨናይል ፡ ዴ ፡ ሊንኩዌንትስ ፡ (በአዲስ ፡ አበባ ፡ የወጣት ፡ ወንጀለኞች ፡ ቤት)" በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፡ ተመልከት ።

54. የተጠቀሰውን ፡ የራደሉ ፡ ጽሑፍን ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ተመልከት ።

ለተኛው፡ የኢትዮጵያ፡ የአምስት፡ ዓመት፡ የእድገት፡ እቅድ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። [55]
እዚህ ፡ ግብ፡ ለመድረስ፡ አሁን፡ አዲስ፡ ሕግ፡ እንዲወጣ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። [56]
በሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የማኅበራዊ ፡ በጎ ፡ አድ
ራጎት ፡ ክፍል ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የመጀመሪያውን፡ እርምጃ ፡ በመውሰድና ፡ ጥረቱን
በማስተናበር ፡ ስለ ፡ ልጆች፡ መልካም (በጐ) አጠባበቅ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ የሕግ
ረቂቅ ፡ በማሰናዳት ፡ ላይ ፡ ነው ። የፖሊስ ፡ ክፍልም፡ የልጆችን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመ
ለከት ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከፍቷል ። እንደዚሁም ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡
ማዘጋጃ ፡ ቤትና ፡ ይህንኑ ፡ የመሰሉ ፡ ድርጅቶች ወ. ወ. ክ. ማ.ና ፡ እስካው
ቶች ፡ የመገናኛ ፡ ቦታዎችን ፤ ክበቦችንና ፡ የወጣቶች፡ አእምሮና ፡ ሕዋሳት ፡ የሚ
ፍታቱባቸውንም ፤ የሚሠለጥኑባቸውን ፡ ነገሮች፡ የሚሰጡ ፡ አስፈላጊ ፡ ድርጅቶ
ችን ፡ ማቋቋም ፡ ጀምረዋል ። አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ አጥፊዎች ፡ የሚፈጸሙ
ወንጀሎችን ፡ መከላከልና ፡ ለነዚህም ፡ ወጣቶች ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡
መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዘገየች ፡ ብትሆንም ፡ ችግሩ ፡ አስጊ ፡ ደረጃ ፡
ላይ ፡ ሳይደርስ ፡ ጥሩ ፡ አጀማመር ፡ መደረጉ ፡ መልካም ፡ ነው ።

## ሠ <u>መደምደሚያ ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡
ጠቅላላ ፡ አቅዋም ፡ የሚያመለክት ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ነው ። ስለተጻፈው ፡ ሕግ
ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ዝርዝር ፡ ሐተታ ፡ ለመጨመር ፡ ይቻላል ፤ ስለ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
አፈጻጸሙ ፡ ግን ፡ የሚታወቀው ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እን
ደታየው ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተገለጹት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፤ እንዲሁም
ከፍተኛ ፡ ዓላማዎች ፡ መካከልና ፡ በቅጣቱ ፡ አቅድ ፡ ውስጥ ፡ በሚፈጸሙበት ፡ እኳ
ኋን ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩነት ፡ አለ ። ይኸ ፡ ልዩነት ፡ በሚያጠግብ ፡ አኳኋን
እየተደመሰሰ ፡ እንዲሄድ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ በጥልቅ ፡ ጥናት ፡ የተደገፈ ፡ ምር
ምርና ፡ የተስፋፋ ፡ የትምህርት ፡ ዕድል ፡ እንዲኖር ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። መል
ካም፡ አጀማመር ፡ ተደርጓል ። የነዚህም ፡ ችግሮች፡ መኖር ፡ በበለጠ ፡ እየታወቀ ፡
መሄድና ፡ ችግሮቹ ፡ በመጨረሻ ፡ መፍትሔአቸውን ፡ አግኝተው ፡ ልማት ፡ በኢ
ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የብዙዎች ፡ ፍላጐት ፡ መሆኑም ፡ የሚያበረታታ ፡ ነው ።

55. (አዲስ ፡ አበባ ፡ ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፱) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷ ።

56. ከላይ ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ በቁጥር ፡ ፵፮ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወጣት አጥፊዎች ፡ ችሎት ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ቁ.፩፻፷፪/፶፫ ዓ. ም. የወሰነውን ፡ ተመልከት ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ መጨረሻ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። "ፍርድ፡ ቤቱ ፡ የዚሁ፡ ፍርድ ፡ የአጭር ፡ ማጠቃለያ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወጣት ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ለመፍረድ ፡ የሚያጋጥመውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በኩል ፡ ለተከበሩ ፡ የአገር፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርና ፡ ለተከበሩ ፡ የፍርድ ፡ ሚን ስትር ፡ እንዲላክ ፡ ያሳስባል ።"